# አይሲስ እስላማዊ ነውን?









ኑረዲን ኢብን አል-መሲህ

# ለይሴሰ እስላማዊ ነውን?

## ለዘጋጅ፡ ኑሪዲን ኢብን ለል-መሲህ

### 2ኛ ዕትም

ልዩ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመታት ሁሉ እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ናቸው፡፡

ልዩ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በኢት. መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር በ1954 ከተዘጋጀው የአማርኛ ትርጉም ነው፡፡

የቁርአን ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በነጃሺ አሳታሚ ድርጅት ከታተመው የአማርኛ ትርጉም ነው፡፡

የአዘጋጁ መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

© 2015 Nuredin Ibn al-Massih

አስተያየቶቻችሁ በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ይደርሱናል፡

christopherdgm@gmail.com

# መቅድም

ይህ ጊዜ ዓለማችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተናጠችና እየታመሰች ያለችበት ጊዜ ነው፡፡ ሰላሟን እያናጉ የሚገኙ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ቢኖሩም አብይ መንስኤው ግን በእስልምና አንፅሮተ ዓለም ላይ የተመሠረተው የአክራሪነት አስተሳሰብ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በሦርያ፣ በኢራቅ፣ በየመን፣ በሊብያ፣ በናይጄሪያ፣ በሶማሊያ፣ በፓኪስታን፣ በአፍጋኒስታንና በሌሎችም ብዙ የዓለም አገራት የሚታዩት ሁኔታዎች ይህንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑ በተደጋጋሚ ይነገረናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ስብከቶች ከእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ብቻ ሳይሆን እምነቱን ከማይከተሉ የሽብር ተግባራቱ ሰለባዎች ከሆኑት ግለሰቦችና አገራት ዘንድ መሰማታቸው ጉዳዩን አደናጋሪ ያደርገዋል፡፡ ‹እስልምና የሰላም ሃይማኖት ከሆነ እምነቱን አክርረው የያዙ ሙስሊሞች ስለምን እጅግ ሰላማውያን ከመሆን ይልቅ እጅግ ነውጠኞች ሆኑ? እንዲህ ዓይነት ተግባራትስ ስለምን የእምነቱ መታወቂያዎች ሆኑ?› በማለት ተገቢ የሆነውን ጥያቄ የሚሰነዝሩ ወገኖች *እስላሞፎቢያ* የሚል "የአዕምሮ ህመም" ስም ይለጠፍላቸዋል፡፡ እስልምና የሰላም ሃይማኖት እንዳልሆነ በድፍረት የሚናገሩ ሰዎች ሕይወታቸውን ለአደጋ ያጋልጣሉ፡፡ ስመ ጥር ግለሰቦች እስልምና የሰላም ሃይማኖት አለመሆኑን ሲናገሩ ከተደመጡ ፅንፈኛ ሙስሊሞች አደባባይ በመውጣት ንብረት ያወድማሉ፣ የንፁኀንን ደም ያፈስሳሉ፣ በእምነት ተቋማት ላይ ቦምብ ይጥላሉ፣ የሰላም ሃይማኖት መሆኑን ለማሳመን ሰላምን ያደፈርሳሉ፡፡ የእነዚህ ወገኖች ተግባርና ስለ እምነቱ የሚሰበከው ስብከት አራምባና ቆቦ ሆኖብን ግራ ተጋብተን ሳናበቃ እስልምና የሰላም ሃይማኖት አለመሆኑንና "ካፊሮችን[1] ማሸበር" እስላማዊ መሆኑን የሚናገሩ ሙስሊም ሊቃውንት ይገጥሙናል፡፡ በኒውዮርክ መንትያ ሕንፃዎች ላይ ጥቃት በተፈፀመ ማግስት የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ደብሊዩ ቡሽ እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን መናገራቸውን ተከትሎ አቡ ቀታዳ የተሰኘ በጂሃድ የሚያምን ሙስሊም አስተማሪ የሚከተለውን ብሎ ነበር፡- "ፕሬዚዳንት ቡሽ በእስልምና ስም የሚደረገውን የጂሃድ ሽብር የሚደግፍ ምንም ዓይነት ነገር በቁርአን ውስጥ አለመኖሩን መናገሩ በእጅጉ አስገርሞኛል፡፡ ለመሆኑ እርሱ የሆነ ዓይነት የእስልምና ሊቅ ነውን? እንዲያው በእድሜ ዘመኑ ቁርአንን አንብቦ ያውቃልን?"[2]

በእስላም አገራት የሚገኙት ብዙ ሙስሊም ሊቃውንት እስልምና የሰላም ሃይማኖት አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡ በምዕራብ አገራትና አገራችንን በመሳሰሉ የሙስሊሞች ቁጥር ከአጠቃላዩ የሕዝብ ቁጥር በሚያንስባቸው አገራት ውስጥ የሚገኙት ደግሞ እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን ይሰብካሉ፡፡ የፖለቲካ መሪዎቻችንና የሃይማኖት አባቶቻችንም ከእነርሱ ጋር ይስማማሉ፡፡ እውነቱ የቱ ነው? ማንን እንስማ? የቱን እንቀበል? ከዚህ ግራ መጋባት ለመውጣት እስላማዊ የሃይማኖት መጻሕፍትን ማጥናት አማራጭ የሌለው በመሆኑ ሕዝባችን እውነቱን አውቆ መፍትሄ መፈለግ ይችል ዘንድ ይህችን አነስተኛ ጽሑፍ አዘጋጅተናል፡፡ አውራ ምስክሮቻችንንም የእስልምናን ቅዱሳት መጻሕፍት አድርገናል፡፡

ከፊት ለፊታችን ከባድ አደጋ የተጋረጠ ቢሆንም ብዙዎቻችን የአደጋውን ግዝፈት ማየት አለመቻላችን ወይም ለማየት አለመፈለጋችን የሚያሳዝን ነው፡፡ በአክራሪዎች በዚህች አገር ውስጥ ለደረሱት ጉዳቶች የኛ ቸልተኝነትና ዝምታ አስተዋፅዖ ማበርከቱን መካድ አንችልም፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ነገሮች ከልክ አልፈው

---

[1] አክራሪ ሙስሊሞች ከእምነታቸው ውጪ የሆነውን እና ከአቋማቸው ጋር የማይስማማውን ማንኛውንም የሚጠሩበት የንቀት አጠራር ነው፡፡ ትርጓሜውም ከሃዲ ማለት ነው፡፡ ቃሉ በቁርአን ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡

[2] Mark Durie, The Third Choice, Islam, Dhimmitude and Freedom, 2010, p. 155

አገሪቱ ከገደሉ አፋፍ ደርሳ ከመውደቋ በፊት እግዚአብሔር መንግሥትን ባያነቃ ኖሮ መፃዒ እጣ ፋንታችን ምን ሊሆን እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን የማስታገሻ እርምጃ እንደተወሰደ እንጂ ትክክለኛ መፍትሄ እንደተሰጠ በልበ ሙሉነት መናገር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የህመሙ ምልክት እንጂ መንስኤው አልታከመምና፤ መንስኤው እስካልታከመ ድረስ ደግሞ ጊዜ ጠብቆ መልሶ ማገርሸቱ የማይቀር ሃቅ ነው፡፡ የአክራሪነት ሥረ መሠረት በቁርአን፣ በሐዲሳትና በሌሎች እስላማዊ ምንጮች ውስጥ ሰፍረው የሚገኙት ትምህርቶች መሆናቸውን መካድ አያዋጣንም፡፡ ሽብርተኝነት የዛፉ ፍሬ በመሆኑ ሥራ መሠራት ያለበት ከፍሬው ይልቅ በግንዱ ላይ ነው፡፡ ይህንን የተረዱት የግብፁ ፕሬዚዳንት አብዱል ፈታህ ኧል-ሲሲ የዓለም ግምባር ቀደም እስላማዊ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ በሚነገርለት በአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ሙስሊም ሊቃውንት ፊት ያደረጉት ዓለምን ያስደመመ ንግግር ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል፡፡ ፕሬዚዳንቱ ያለ ምንም መሸፋፈን ችግሩ የሚገኘው እድሜ ጠገብ በሆኑት እስላማዊ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መሆኑን በማስገንዘብ በዓለም ላይ ለሚገኘው የሽብርተኝነት ችግር መፍትሄ እንዲመጣ ከተፈለገ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት መስተካከል እንዳለባቸው ጥብቅ ማሳሰብያ ሲሰጡ ተደምጠዋል፡፡ የእምነቱ ተከታዮች "በዓለም ላይ የሚገኙትን ሕዝቦች ሁሉ በማጥፋት እራሳቸው ብቻ ለመኖር መፈለጋቸው" የሚያስከትለውን አደጋ በመጠቆም የማስጠንቀቂያ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ የሚከተለው ከንግግራቸው ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው፡-

> ... እዚህ ጋ እየተናገርኩ ያለሁት የእምነት አባቶችን ነው፡፡ እየተጋፈጥን ስላለነው ነገር በአንክሮ ማሰብ ያስፈልገናል - በእርግጥ ይህንን ጉዳይ ከዚህ ቀደም አንድ ሁለት ጊዜ አንስቻለሁ፡፡ በጣም ክቡርና ቅዱስ አድርገን የያዝነው አስተሳሰብ አጠቃላይ ኡማውን [እስላማዊውን ማሕበረሰብ] ለዓለም ማሕበረሰብ የጭንቀት፣ የአደጋ፣ የግድያና የጥፋት ምንጭ እንዲሆን ማድረጉ የማይታመን ነው፡፡ ይህ ሊሆን አይችልም!
>
> ያ አስተሳሰብ - ሃይማኖት እያልኩ አይደለም ነገር ግን አስተሳሰቡ - ከእርሱ ማፈንገጥ የማይቻልበት ደረጃ ላይ እስከንደርስ ድረስ ለክፍለ ዘመናት አክብረን የያዝነው የመጻሕፍትና የአስተሳሰብ ስብስብ መላውን ዓለም እየተፃረረ ይገኛል፡፡ ዓለምን በሞላ እየተፃረረ ነው!
>
> እነዚህን ቃላት እዚህ በአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ፣ በዚህ የሊቃውንትና የኡላማ ጉባኤ ፊት እየተናገርኩ ነው - አሁን እየተናገርኩ ያለሁትን ነገር በተመለከተ ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ በፍርዱ ቀን ስለ እውነተኛነታችሁ ምስክር ይሁንባችሁ፡፡
>
> እየነገርኳችሁ ያለሁትን ይህንን ሁሉ ነገር በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ተጠምዳችሁ የምትኖሩ ከሆነ ልትረዱት አትችሉም፡፡ በትክክል መገምገም እንድትችሉና የበለጠ አብርሆት ካለው ፅንፍ ማየት እንድትችሉ የቀደመውን አስተሳሰብ መጣል ያስፈልጋችኋል፡፡
>
> ደግሜ ደጋግሜ እላለሁ ሃይማኖታዊ አብዮት ያስፈልገናል፡፡ እናንተ ኢማሞች በአላህ ፊት ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡ መላው ዓለም፣ እደግመዋለሁ መላው ዓለም የእናንተን ቀጣይ እርምጃ እየተጠባበቀ ይገኛል... ምክንያቱም ይህ ኡማ እየፈረሰ ነው፣ እየወደመ ነው፣ እየጠፋ ነው - እየጠፋ ያለው ደግሞ በገዛ እጃችን ነው፡፡[3]

በዚህ ንግግር ውስጥ ፕሬዚዳንት ኧል-ሲሲ በእስላማዊ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተሰገሰገው የነውጠኝነት አስተሳሰብ የዓለም ስጋት ምንጭ መሆኑን በግልፅ አስረድተዋል፡፡ በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ

---

[3] በቪድዮ የተደገፈ ሙሉ ንግግራቸውን በዚህ አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡-
http://www.raymondibrahim.com//from-the-arab-world/egypts-sisi-islamic-thinking-is-antagonizing-the-entire-world/ (Accessed on 19/05/20015)

እንደምንመለከተው የሽብርተኝነት ሥረ መሠረት እስላማዊ መጻሕፍት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ የሽብርተኝነት ምንጭ እስላማዊ ትምህርት መሆኑን ለማስረዳት ሌይኤስ የተሰኘው የሽብር ቡድን እየፈፀማቸው የሚገኙት የሽብር ተግባራት በእስላማዊ ምንጮች የተደገፉ መሆናቸውን ማስረጃዎችን በመጥቀስ እናሳያለን፡፡ ይህንን የምናደርግበት ምክንያት ሽብርተኝነት ምንጩ በትክክል ታውቆ መፍትሄ እንዲፈለግ ለማመልከት እንጂ የማንንም እምነት ለማብጠልጠልና ለመንቀፍ አይደለም፡፡ ይህ ማለት ግን ለከንቱ ውዳሴ ብለን እውነትን እናመቻምቻለን ማለት አይደለም፡፡ ለምንናገረው ነገር ማስረጃ መስጠትም ሙያዊ ግዴታችን ነው ብለን እናምናለን፡፡ ስለሆነም ቅሬታ የሚገባው ሰው ካለ ማስረጃዎቹ እውነት መሆን አለመሆናቸውን በጥንቃቄ መርምሮ ካረጋገጠ በኋላ አስተያየቱን እንዲሰነዝር እንጠይቀዋለን፡፡

ተቃውሟችን ያነጣጠረው በግለሰቦችና በየትኛውም የሃይማኖት ማሕበረሰብ ላይ ሳይሆን የእስልምናን ቅዱሳት መጻሕፍት ተተግኖ ዓለምን እያመሰ በሚገኘው የፖለቲካ አይዲዮሎጂ ላይ ነው፡፡ እኛ የፍቅርና የሰላም እንጂ የጥላቻና የብጥብጥ መልዕክት የለንም! በመስቀል ላይ ቅዱስ ደሙን ያፈሰሰልን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን አላስተማረንም! ሆኖም ነገሮችን በማድበስበስ መፍትሄ ሊመጣ ይችላል የሚል እምነት የለንም፡፡ ስለዚህ እውነትን ያለ ፍርሃት በፍቅር እንናገራለን፡፡ ካለማወቅም ይሁን ከፖለቲካዊ ትክክለኝነት (Political Correctness) በመነጨ አስተሳሰብ እስላማዊ መጻሕፍት ሰላምን እደሚያስተምሩ በመስበክ ለእስልምና ጥብቅና ሲቆሙ የነበሩ ወገኖች ይህንን ማድረጋቸው ምንም አልፈየደም፡፡ አንድን ከሥነ ምግባር የወጣ ሰው ሥነ ምግባሩ ጥሩ እንደሆነ ደጋግሞ በመንገር ፀባዩን እንዲያርም ማድረግ እንደማይቻል ሁሉ ሽብርን የሚሰብክ ሃይማኖት ሰላምን እንደሚሰብክ በመናገር ሰላማዊ ማድረግ አይቻልም፡፡ ይልቁኑ ስህተቱን ነቅሶ በማውጣት እንዲያስተካክል መንገር እንጂ መፍረግረግና መለማመጥ አጥፊው የልብ ልብ እንዲሰማው ማድረግ ነው፡፡ እውነትን ሸሽጎ ውሸትን በመናገር ችግሩን ማፈርጠም መፍትሄ አይሆንም፡፡ የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ንግግሮች ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጡ ይቅርና ጊዜያዊ መፍትሄ እንኳ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ የሃይማኖት አባቶችና የፖለቲካ መሪዎች የእስልምናን ሰላማዊነት አጥብቀው ቢሰብኩንም ችግሮች እየተባባሱ ሄዱ እንጂ ሲቀንሱ አልታዩም፡፡ እውነትን በመናገር ሊፈጠር የሚችለውን ጊዜያዊ ችግር በመፍራት ዝንተ ዓለም በሽብር እየተናጡ ከመኖር እውነቱን አፍረጥርጦ በመናገር ዘላቂ መፍትሄ መፈለግ ይበጃል፡፡ "ጅቡ እግሬን እየበላው ነውና እንዳይሰማን ዝም በል" እንዳለው ሞኝ ሰው መሆን ይበቃናል፡፡

# መግቢያ

የኢራቅና የሦርያ እስላማዊ መንግሥት (ISIS) ወይም እስላማዊ መንግሥት (IS)፣ በአረብኛ ደግሞ *ዳዕሽ* የተሰኘው የሽብር ቡድን የተስፋፋው በሦርያ የተነሳው ሕዝባዊ አመፅና በኢራቅ ያለው ደካማ የመንግሥት ይዞታ በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ከዚያ ቀደም ብለው በነበሩት ዓመታት ድርጅቱ የአልቃኢዳ ክንፍ ሆኖ በአካባቢው ይንቀሳቀስ ነበር፡፡ አቡ ሙሳብ አል ዛርቃዊ የተሰኘው መሪው በአሜሪካ የአየር ጥቃት በ2006 እስከተገደለበት ጊዜ ድረስ የንፁኀን ወገኖችን አንገት እየቀላ ቪድዮዎችን ያሰራጭ ነበር፡፡ ይህ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ከኢራቅ ጦርነት በኋላ የተቀዛቀዘ ቢሆንም የሽብር ቡድኑ አይኤስ በሚል ሥም እንደገና ተመልሶ ከመጣ በኋላ መሰል ቪድዮዎችን በተሻለ ጥራትና በብዛት እየቀረፀ መልቀቁን ተያይዟል፡፡ ከሦርያና ከኢራቅ ባሻገርም ኢትጵያውያንን ጨምሮ በብዙ አገራት ንፁኀን ዜጎች ላይ የግፍ ክንዱን አሳርፏል፡፡

የአይኤስ መኖር ለዓለም ሕዝብ ይፋ የሆነው ከሦርያ ወደ ኢራቅ በመግባት በአስገራሚ ፍጥነት የኢራቅን ሰራዊት እየበታተነ ብዙ አካባቢዎችን መቆጣጠር በጀመረበት ወቅት ነበር፡፡ ይህም ውስጥ ለውስጥ ለረጅም ጊዜያት ዝግጅት ሲያደርግ እንደነበርና የጥንካሬ ደረጃውን ካረጋገጠ በኋላ በራሱ ፈቃድ ሀልዎቱን ይፋ ማድረጉን ያመለክታል፡፡ በአካባቢው ሽብርተኛ ድርጅቶች እንደሚንቀሳቀሱ ቢታወቅም ነገር ግን ይህን ያህል ጥንካሬ፣ አደረጃጀትና ትጥቅ ያለው ሽብርተኛ ድርጅት መኖሩ ለምዕራባውያኑ የስለላ ተቋማት እንኳ ሳይቀር ድንገተኛና አስደንጋጭ እንደነበር መረዳት አያዳግትም፡፡ ይህም የቡድኑ አደገኛነት ምን ያህል እንደሆነ አመላካች ነው፡፡ አቡቀለምሲሳዊ (Apocalyptic) ራዕይ ያለው የሽብር ቡድኑ ዓለምን ሁሉ በእስልምና ቁጥጥር ስር የማድረግ ዓላማ እንዳለው በመግለፅ ኢትዮጵያን የሚያካትት *የኸሊፋ* ካርታ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ወቅት ይህ ቡድን እስልምናን እንደማይወክልና ድርጊቱም ደግሞ እስላማዊ እንዳልሆነ፣ እንዲያውም እስልምናን የሚፃረር እንደሆነ ሲነገር እንሰማለን፡፡ ነገር ግን የብዙዎችን ሕይወት እየቀጠፈ የሚገኘው ይህ የነፍሰ ገዳዮች ስብስብ ተግባር እውን እስልምናን የሚፃረር ነውን? እስላማዊ ጽሑፎችስ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ይኮንናሉ ወይንስ ያበረታታሉ? አይኤስ እስላማዊ ከሆነ ለምንድነው ሙስሊሞችም ጭምር ሰለባዎቹ የሆኑት? ብዙ ሙስሊሞችስ ለምን ይሆን ድርጊቱን በመኮነን እስላማዊ አለመሆኑን የሚገልፁት? የፖለቲካ መሪዎች ለምንድነው የእስልምናን ሰላማዊነት የሚሰብኩት? በዚህ ጽሑፍ ለነዚህ እና እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች ምላሾችን እንሰጣለን፡፡ ሽብርተኝነትን በተመለከተ የመፍትሄ ሐሳቦችን እንጠቁማለን፡፡

❶

# አይኤስ እስላማዊ ነውን?



አቡበከር አል ባግዳዲ፡ የሽብር ቡድኑ ዋና መሪ

ይህ መልስ የሚሻ የብዙዎች ጥያቄ ነው፡፡ በአጭር ቃል አይኤስ እስላማዊ ነው፡፡ አባላቱ በእስልምና ያደጉና ብዙዎቹ እስልምናን በሚገባ ያጠኑ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ አቡበከር አል-ባግዳዲ (ኢብራሂም አወድ ኢብራሂም አል በድሪ) የተሰኘው መሪያቸው በእስላማዊ ጥናቶች ከባግዳድ ዩኒቨርሲቲ ፒ.ኤች.ዲ. የተቀበለ ነው፡፡[4] የኢትዮጵያውያኑን ጭፍጨፋ በሚያሳየው ቪድዮ ውስጥ ሲናገር የሚታየው የሰዑዲ አረብያ ዜግነት እንዳለው የሚነገረው አነስ አል-ነሸዋን (የሚስጥር ሥሙ አቡ ማሊክ አል-ተሚሚ) ደግሞ በሸሪኣ ህግ የማስተርስ ድግሪ ያለው ነው፡፡[5] እነዚህ ሰዎች እስልምናን የማያውቁ፣ በስሜት የሚነዱ ስራ አጦች አይደሉም፡፡ እነዚህ እስልምናን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ለእምነታቸው ሲሉ የተሻለውን ኑሯቸውን በመተው ጦርነት ውስጥ የገቡ ሙስሊም ሊቃውንት ናቸው፡፡ ያልተማሩና በአንድ ሰው ስብከት በቀላሉ የሚወሰዱ መሃይማንም አይደሉም፡፡ ብዙዎቹ በምዕራብ አገራት ውስጥ ኑሯቸውን የመሰረቱ፣ ፊደል የቆጠሩና ጥሩ ገቢ የነበራቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የአይኤስ ዋና አራጅ የሆነው ሙሐመድ ኤምዋዚ[6] የኮምፒውተር ሳይንስ ባለሙያና የእንግሊዝ ዜግነት ያለው ሰው ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሰዎች እስልምናን የማያውቁ፣ ያልተማሩ ተራ ወሮበሎች አድርጎ መፈረጅ እውነታን የሚፃረር ነው፡፡

አይኤስ የሚጠቀሟቸው ቃላት (Vocabulary) እስላማዊ ናቸው፡፡ *ደቢቅ* የሚለው የመጽሔታቸው ሥያሜ በሦርያ ውስጥ ከሚገኝ የቦታ ሥም የተወሰደ ሲሆን በእስላማዊ ትንቢቶች መሠረት በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል የመጨረሻው ጦርነት ይደረግበታል ተብሎ የተነገረ ቦታ ነው፡፡[7] *አል-ፉርቃን* የሚለው የቪድዮ ፕሮዳክሽን ሥያሜ "መመርያ" የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን የቁርአን ሌላኛው መጠርያ ነው፡፡ ቃሉም በቁርአን ውስጥ ለበርካታ ጊዜያት ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ የኢትዮጵያውያን ስደተኞቹን ጨምሮ የእርድ ቪድዮዎችን እየቀረፀ የሚያሰራጨው ይኸው የአይኤስ የሚድያ ክንፍ ነው፡፡

---

[4] http://www.wikipedia.org/wiki/Abu_Bakar_al-Bagdadi (Accessed on 5/18/2015)

[5] http://www.geopolintelligence.com/isis-video-shows-militants-killing-groups-of-ethiopian-christians (Accessed on 5/18/2015)

[6] አሊ አዶሩስ የተሰኘው የቅርብ ጓደኛው ለሽብር ተግባር ሲንቀሳቀስ ተይዞ ኢትዮጵያ ውስጥ በእስር ላይ ይገኛል http://www.dailymail.co.uk/news/article-2983850/The-Londoner-went-Tanzanian-safari-Jihadi-John-currently-jail-Ethiopia-terrorism-offences.html (Accessed on 5/19/2015)

[7] Sahih Muslim, 41:6924

የአይኤስ ሥያሜ፣ የአባላቱ መጠርያዎች፣ ቅፅል ሥሞቻቸው፣ የዘመቻ ሥያሜዎቻቸው፣ ወዘተ. ሁሉ እስላማዊ ናቸው:: እስላማዊ ያልሆነ ንግግር አይጠቀሙም::

የአይኤስ ጥቁሩ ባንዲራ የጂሃድ ባንዲራ ነው:: በላዩ ላይም በአረብኛ ተጽፎ የምናየው ሌላ ነገር ሳይሆን ሸሃዳ (የእስልምና የእምነት አቋም) ነው:: *ላ ኢላ ሀኢለላ መሐመደን ረሱልአላህ* (ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም መሐመድም መልእክተኛው ናቸው) የሚል ነው:: ይህ የአንድ ሙስሊም የመጀመርያና የመጨረሻ ቃሉ ነው:: በእስላማዊ ትንቢቶች መሠረት ይህንን ጥቁር ባንዲራ የያዘ የጂሃድ ቡድን በመጨረሻው ዘመን ይነሳል:: ሙስሊሞችም ሁሉ ይህንን ቡድን መቀላቀል ይኖርባቸዋል::



በአይ ኤስ ባንዲራ ላይ የሚገኘው ጽሑፍ ሸሃዳ (የእስልምና የእምነት አቋም) ነው:: ላ ኢላ ሀኢለላ መሐመደን ረሱልአላህ (ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም መሐመድም መልእክተኛው ናቸው) ይላል::

አይኤስ አለባበሳቸው፣ አመጋገባቸው፣ የጋብቻ ሁኔታቸው፣ ጢም አቆራረጣቸው፣ ሙስሊም ካልሆኑት ሰዎች ጋር ያላቸው መስተጋብር፣ የማህበረሰብ አደረጃጀታቸው፣ ባጠቃላይ የኑሮ ዘይቤያቸው ሁሉ ፍፁም እስላማዊ ነው:: ከእስልምና ጋር የሚጣረስ፣ በመሐመድ ሱና (ምሳሌነት) ያልተረጋገጠ፣ በቁርአንና በሐዲሳት ያልፀደቀ ምንም ነገር የላቸውም::

ለሚያደርጉት ለእያንዳንዱ ነገር ቁርአንና ሐዲሳትን ጨምሮ እስላማዊ ምንጮችን ይጠቅሳሉ:: የቁርአንን አተረጓጎም በተመለከተ የሱኒ ነባር ሐታቶችን (Classical Sunni Commentators) ይጠቀማሉ:: ምናልባት እስላማዊ ቃላትን መጠቀማቸውና እስላማዊ የኑሮ ዘይቤዎችን መከተላቸው በራሱ ትክክለኛ ሙስሊሞች ሊያደርጋቸው አይችልም የሚል ሐሳብ ሊነሳ ይችላል:: ይህ አባባል የተወሰነ እውነታነት አለው:: የእነዚህ ሰዎች ድርጊቶች በእስላማዊ ቅዱሳት መጻሕፍት መደገፋቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ ትክክለኛ ሙስሊሞች ናቸው ብሎ መናገር አዳጋች ነው:: ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የሚፈፅሟቸው ነገሮች ሁሉ ፍፁም እስላማዊ መሆናቸውን ቁርአንና ሌሎች እስላማዊ ምንጮችን ያነበበ ሰው ሁሉ የሚያውቀው እውነታ ነው:: ከእስልምና የወጣ ምንም ነገር አላደረጉም:: ነገር ግን ችግሩ ብዙ ሰዎች ስለ እስልምና ያላቸው መረጃ በመገናኛ ብዙኃን በሚነገሩ ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን በተከተሉ ንግግሮችና ሙስሊም አቃቤ እምነታውያን በሚናገሯቸው የተቀመሙ ንግግሮች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው:: በዚህ ብዙ ድምፆች ውዥንብሮችን በሚፈጥሩበት ዘመን ዋናዎቹን ምንጮችና የእምነቱን መስራች የመሐመድን ሕይወት ካላጠናን በስተቀር የእስልምናን ትክክለኛ ገፅታ ማወቅ ቀላል አይሆንም:: የሚፈፀሙ የሽብር ጥቃቶችንም የእምነቱን ሽፋን በመጠቀም የተወሰኑ የግል ጥቅም አሳዳጆች ወይንም እምነቱን በተሳሳተ መንገድ የተረዱ ሰዎች እንደሚፈፅሙት የውንብድና ተግባር ልንቆጥር እንችላለን:: ይብዛም ይነስም እንዲህ ዓይነት ሰዎች በሁሉም እምነቶች ውስጥ እንደሚገኙ ይታመናልና::

ዛሬ አንድ ክርስቲያን ተነስቶ በእምነቱ ሥም የሽብር ተግባር ቢፈፅም ድርጊቱ ክርስቲያናዊ አለመሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ ማስረዳት እንችላለን:: ለድርጊቱ ማፅደቂያ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች

ቢጠቅስ ከአውድ ውጪ እንደጠቀሰና በተሳሳተ መንገድ እንደተረጎመ በማስረዳት ልናርመው እንችላለን፡፡ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ የሚል የማያወላዳ ትዕዛዝ ሰጥቶናልና፡-

> *ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።* ማቴዎስ 5፡43-48

አንድ ክርስቲያን ከዚህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ በማፈንገጥ በስመ እግዚአብሔር የሽብር ድርጊቶችን ቢፈፅም በክርስቲያኖች ዘንድ በፅኑ ይወገዛል፡፡ ክርስቲያን ተብሎም ሊጠራ አይችልም፡፡ በእስልምና ግን እንዲህ አይደለም፡፡ እውነተኛና ትክክለኛ የመሐመድ እስልምና አይኤስን በመሳሰሉት የጥላቻ ቡድኖች እየተተገበረ የሚገኘው እንጂ በተከሸኑ ቃላት ተሸሞንሙኖ በሚድያዎች፣ በፖለቲከኞችና በሙስሊም አቃቤ እምነታውያን የሚሰበከው ክርስትና የተነሳ እስልምና አይደለም፡፡ ቁርአንና የመሐመድን ግለ ታሪክ ቀረብ ብለን ብንመለከት ነቢዩ መሐመድ በዳዕሾች ተሠግዎ በዘመናችን እንደተገለጡ ማስተዋል እንችላለን፡፡ በአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ የእስልምና ታሪክ ፕሮፌሰር የነበሩትና እስልምናን በመተው ክርስትናን የተቀበሉት ማርክ ገብርኤል (በቀድሞ *ሥማቸው ሙስጠፋ*) የቁርአንን አስተምህሮና የእስልምናን ታሪክ በተመለከተ የሚከተለውን ይላሉ፡-

> በቁርአን ውስጥ የተገለጠው አምላክ፣ አላህ አፍቃሪ አባት አይደለም፡፡ ሰዎችን በተሳሳተ መንገድ መምራት ይፈልጋል (ሱራ 6፡39፣ 126)፡፡ በእርሱ ወደ ተሳሳተ መንገድ የተመሩትን አይረዳቸውም (ሱራ 30፡29)፡፡ ገሃነምንም ለመሙላት ይጠቀምባቸዋል (ሱራ 32፡13)፡፡ እስልምና በሴቶች ላይ፣ ሙስሊም ባልሆኑት ላይ፣ በክርስቲያኖች ላይ እና በተለይም ደግሞ በአይሁዶች ላይ አድሎን በማድረግ የተሞላ ነው፡፡ ጥላቻ የኃይማኖቱ አካል ነው፡፡ የእኔ ልዩ የጥናት መስክ የሆነው የእስልምና ታሪክ የደም ወንዝ በመባል ብቻ ነው ሊገለፅ የሚችለው፡፡[8]

## ሁለቱ የማደናገርያ ጥቅሶች

የአክራሪ እስልምና ትክክለኛ ገፅታ ገሃድ እየወጣ ባለበት በዚህ ወቅት ብዙ ወገኖች እነዚህ ቡድኖች እስላማዊ አለመሆናቸውንና እስልምናም የሰላም ሃይማኖት መሆኑን እየሰበኩ ይገኛሉ፡፡ እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑንም ለማሳየት ከቁርአን ውስጥ የተወሰኑ ጥቅሶችን ከታሪካዊና ምንባባዊ አውዳቸው ውጪ በመጥቀስ ሊያሳምኑን ይሞክራሉ፡፡ አሳዛኙ ነገር ብዙ ሰዎች በነዚህ ከንቱ ስብከቶች ተታልለው የአክራሪ እስልምናን ፀረ ሰላም መሆን መጠራጠራቸው ነው፡፡ የእስልምናን ሰላማዊነት ለማስረዳት በተደጋጋሚ የሚጠቀሱት ሁለት ጥቅሶች ሲሆኑ እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

*በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡ (ሱራ 2፡256)*

ይህ ጥቅስ ቁርአንን የማያነበውንና የእስልምናን ታሪክና አስተምህሮ በወጉ የማያውቀውን ህዝብ ለማደናገር በእጅጉ እያገለገለ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የቁርአን ሐታቾች እንደሚናገሩት ይህ ጥቅስ ጊዜው አልፎበታል፡፡ እስልምና *ናሲክ* የተሰኘ አስተምህሮ አለው፡፡ ናሲክ መሻር የሚል ትርጉም ያለው የአረብኛ ቃል ሲሆን በዚህ አስተምህሮ መሠረት ሁለት እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ የቁርአን ጥቅሶች ቢኖሩ የኋለኛው የፊተኛውን

[8] Mark Gabriel: Islama and Terrorism, 2002, p. 5

ይሸረዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ ኢብን ከሢር የተሰኘ ትልቅ ተቀባይነት ያለው የሱኒ ሐታች የጥቅሱን ትክክለኛ ትርጉም፤ ማለትም ሰዎች እምነታቸውን እንዲቀይሩ ማስገደድ አስፈላጊ አለመሆኑን እንደሚናገር ካብራራ በኋላ እንዲህ ይላል፡- *"… ነገር ግን ይህ ጥቅስ በውጊያ ጥቅሶች ተሽሯል ስለዚህ ሁሉም የዓለም ህዝቦች ወደ እስልምና እንዲመጡ ጥሪ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ማናቸውም ሰዎች ያንን ለማድረግ ፍቃደኛ የማይሆኑ ከሆነ ወይም ጂዝያን ለመክፈል እምቢ የሚሉ ከሆነ እስኪገደሉ ድረስ ውጊያ ሊደረግባቸው ይገባል…"*[9]

አይኤስ ክርስቲያን ኢትዮጵያውኑ የተገደሉበትን ምክንያት ሲገልፅ ጂዝያን ለመክፈል ፍቃደኞች ባለመሆናቸው ይህ ፍርድ እንደተላለፈባቸው ተናግሯል፡፡ ሌሎች ብዙ ሙስሊም ሐታቾች ይህ ጥቅስ በኋለኞቹ መገለጦች መሻሩን ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ ጥቅሱ ካፊሮችን ከማደናገር የዘለለ ጥቅም የለውም፡፡

የእስልምና ሰላማዊነት ለማሳየት የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ ሱራ 5፡32 ላይ የሚገኘው፡- *"ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት (ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው"* የሚለው ነው፡፡ ነገር ግን ሙስሊም ሊቃውንት ይህንን ጥቅስ ከአውድ ውጪ ነው የሚጠቅሱት፡፡ ሙሉ አውዱ እንዲህ ይላል፡- *በዚህ ምክንያት በእስራኤል ልጆች ላይ እነሆ ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት (ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ማለትን ጻፍን፡፡ መልክተኞቻችንም በግልጽ ተዓምራት በእርግጥ መጡዋቸው፡፡ ከዚያም ከዚህ በኋላ ከእነሱ ብዙዎቹ በምድር ላይ ወሰንን አላፊዎች ናቸው፡፡*

የቁርአን ጸሐፊ ይህንን ሐሳብ የቀዳው ከአይሁድ መጻሕፍት ላይ ነው፡፡ ጥቅሱ የሚናገረው ይህ ትዕዛዝ የተሰጠው ለእስራኤላውያን መሆኑን ነው፡፡ ለሙስሊሞች ደግሞ ምን ዓይነት ትዕዛዝ እንደተሰጠ ቀጣዩ አንቀፅ ይናገራል፡- *"የእነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር መባረር ነው፡፡ ይህ በነሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው፡፡ በመጨረሻይቱም ለእነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው፡፡"* ሱራ 5፡35

ቀደም ሲል የተጠቀሰው በጎ ትዕዛዝ የተሰጠው ለእስራኤላውያን ሲሆን በማስከተል የተቀመጠው የጭካኔ ትዕዛዝ ደግሞ ለሙስሊሞች የተሰጠ መሆኑን እናያለን፡፡ አላህንና መልክተኛውን መዋጋት ማለት በእስላማዊ አተረጓጎም መሠረት ማንኛውንም ቁርአንንና እስላማዊ ህግጋትን መፃረር እንዲሁም የመሐመድን ነቢይነት አለመቀበል ማለት ነው፡፡ በምድር ላይ ማጥፋት ደግሞ ለሙስሊም ማህበረሰብ እንቅፋት የሚሆን ማንኛውንም ነገር ማድረግን ያመለክታል፡፡ ይህም ወንጌልን መስበክን ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ "ሂዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚለውን የጌታን ትዕዛዝ በሸሪአ ህግ በሚተዳደር የሙስሊም ማሕበረሰብ መካከል የምንተገብር ከሆነ በሸሪአ ህግ መሠረት ቅጣቱ በጥቅሱ ውስጥ የተዘረዘረው ነው፡፡

"ጅብ እስኪይዝ ያነክሳል" እንደሚለው የአገራችን ብሒል አክራሪ እስልምናም እነዚህን የመሳሰሉ ጥቅሶችን በመጠቃቀስ ምቹ ጊዜ እስኪመጣለት ድረስ ይሸነግላል፡፡ የበላይ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ግን ትክክለኛ ገፅታውን ያሳያል፡፡ በመታረድና ለእርሱ በመገዛት መካከል ያስመርጣል፡፡ ሦስተኛ አማራጭ የለም፡፡

[9] Tafsir of Ibn Kathir, Al-Firdous Ltd., London, 1999: First Edition, Part 3, pp. 37-38

❷

## የአይኤስን እኩይ ተግባራት የሚያፀድቁ እስላማዊ ትምህርቶች

“ማየት የተሳነው ሼኽ” በመባል የሚታወቀው ኦማር አብደልረህማን የዓለም ቁጥር አንድ እስላማዊ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ በሚነገርለት በአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የቁርአን ሥነ-ፍታቴ ፕሮፌሰር ነበር፡፡ ይህ ሰው አል ጂሃድ የተሰኘው እስላማዊ የሽብር ቡድን መንፈሳዊ መሪ የነበረና የፕሬዚዳንት አኑዋር ሳዳትን ግድያ ያቀነባበረ ሲሆን ሊተላለፍበት ከነበረው ብያኔ የንግግር ችሎታውንና ስለ እስላማዊ ምንጮች የነበረውን የላቀ ዕውቀት በመጠቀም ሊተርፍ ችሏል፡፡ ይህ ሰው ከግብፅ ወደ ሱዳን በመሄድ የፕሬዚዳንት ሐሰን አልቱራቢ አማካሪ በመሆንም አገልግሏል፡፡ አልቱራቢ በደቡብ ሱዳናውያን ክርስቲያኖች ላይ ላደረሰው ግፍና ሰቆቃ የዚህ ሰው ክፉ ምክር አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ ይህ ሰው “የጂሃድን ጦርነት ወደ ካፊሮች አገር መውሰድ” በሚል ፍልስፍና መሠረት ወደ አሜሪካ በመሄድ ብዙ ሽብርተኞችን በምድረ አሜካ ካሰለጠነ በኋላ በ1993 ዓ.ም. የተፈፀመውን የዓለም የንግድ ማዕከል የቦምብ ጥቃት አቀነባብሮ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበት በግዞት ይገኛል፡፡

ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ዶ/ር ማርክ ገብርኤል በአንድ ወቅት ከዚህ ሽብርተኛ ጋር ያደረጉትን ንግግር በዚህ መልኩ አስቀምጠዋል፡-

> በ1980 ዓ.ም. በአል-አዝሃር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የመጀመርያ ዓመት ተማሪ ሳለሁኝ የቁርአን ሥነ-ፍታቴ በመባል የሚታወቅ ትምህርት ተምሬ ነበር፡፡ ለእስልምና ያለው ሸክም በተማሪዎች ዘንድ ዝነኛ ያደረገውን ማየት የተሳነውን ሼኽ ትምህርት ለመስማት በወር ሁለት ጊዜ እንሰበሰብ ነበር፡፡ ይህ ሰው አክራሪ ገፅታው በግልፅ ይታይ ነበር፡፡ ክርስቲያኖችን እና አይሁዶችን የሚመለከቱ ጥቅሶችን በቁርአን ውስጥ ባገኘ ቁጥር ክርስቲያኖችን ከሃዲያን አይሁዶችን ደግሞ የእርያ ልጆች በማለት በመጥራት ሀሴት ያደርግ ነበር፡፡ የቀድሞውን የእስልምና ክብር በጂሃድ መልሶ ለማምጣት ፍላጎት እንዳለውም በግልፅ ይናገር ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ጥያቄዎችን እንድንጠይቅ ዕድል ሰጠን፡፡ እኔም ተነስቼ በመቆም ለብዙ ጊዜ ስገረምበት የነበረን አንድ ጥያቄ ጠየቅሁት፡ ለምንድነው ሁል ጊዜ ስለ ጂሃድ የሚያስተምሩን? በቁርአን ውስጥ ስላሉት ስለ ሰላም፣ ፍቅር እና ይቅርታ ስለሚናገሩት ጥቅሶችስ ለምን አንማርም?
>
> ፊቱ ከመቅፅበት ቀላ፡፡ ሲቆጣ ማየት እችል ነበር ነገር ግን ደግሞ ቁጣውን ለመቆጣጠር መምረጡንም አስተዋልኩኝ፡፡ እኔ ላይ ከመጮኽ ይልቅ ሲያደምጡት በነበሩት በአምስት መቶ ተማሪዎች ፊት ሐሳቡን ለመግለፅ ዕድሉን ተጠቀመበት፡፡ ወንድሜ በማለት ጀመረ፤ የጦር ዘረፋዎች የሚል አንድ ሙሉ ምዕራፍ አለ፡፡ ሰላም ተብሎ የተሰየመ አንድም ሱራ የለም፡፡ ጂሃድ እና መግደል የእስልምና ራስ ናቸው፡፡ እነርሱን አውጥተህ ብትጥል የእስልምናን ራስ ቆረጥክ ማለት ነው፡፡ [10]

ፅንፈኛ ሙስሊሞች የበላይነት እንዳላቸው በተሰማቸው ጊዜ ሁሉ ጂሃድ እና እስልምና የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፆች መሆናቸውን ከመናገር ወደ ኋላ ብለው አያውቁም፡፡ ነገር ግን ይህንን እውነታ በግልፅ መናገር እንደሚያስጠቃቸው ከተሰማቸው ጭራቸውን እያወናወኑ በመለማመጥ ይኖራሉ፤ የእስልምናንም ሰላማዊነት ይሰብካሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በዝርዝር የምንመለከታቸውን ስለ ጂሃድ የሚናገሩትንም የቁርአን ጥቅሶች በአደባባይ

[10] Mark Gabriel: Islam and Terrorism, 2002, p 23-24

አያነቧቸውም፡፡ በማስከተል የአይኤስን ኢ-ሰብአዊ ተግባራት የሚያፀድቁ እስላማዊ ትምህርቶችን ከቁርአን፣ ከሐዲሳትና ከመሐመድ ታሪኮች በማመሳከር እንመለከታለን፡፡

## ማስፈራራትና ሽብርን መንዛት




አይኤስ የኢራቅና የሦርያ መንግሥታት ሰራዊቶችን በቀላሉ በታትኖ ሰፊ ግዛቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ መቆጣጠር የቻለው ፍርሃትን በመንዛት ነበር፡፡ አሳቃቂ የጭካኔ ቪድዮዎችንም የሚያሰራጨው በሰዎች ልብ ውስጥ ፍርሃትና ሽብርን ለማስረፅ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ይህንን ስልት ደግሞ በቀጥታ የቀዳው ከመሐመድ ሕይወት መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ የእስልምና ጀማሪ የሆኑት መሐመድ እንዲህ ማለታቸው ተነግሯል፡- *__በሽብር__ ድል ነሺ ተደርጌያለሁ፡፡*[11] በሌላ ዘገባም *__በሽብር__ ኢታገዛለሁ* ማለታቸው ተነግሯል፡፡ ይህም ከሌሎች የቀደሙት ነቢያት ሁሉ ልዩ እንደሚያደርጋቸው በኩራት ተናግረዋል፡፡ [12]

ቁርአንም የእስልምና አምላክ የሆነው አላህ ሽብርን እንደሚነዛ ይናገራል፡-

> *በእነዚያ በካዱት ሰዎች ልቦች ውስጥ አላህ በእርሱ አስረጅ ያላወረደበትን ነገር በአላህ በማጋራታቸው ምክንያት **ፍርሃትን** እንጥላለን፡፡ መኖሪያቸውም እሳት ናት፡፡ የበዳዮችም መኖሪያ ምን ትከፋ! የዒምራን ቤተሰብ ምዕራፍ 3፡151 (በተጨማሪም ሱራ 8፡12፣ 8፡59-60፣ 33፡25-27፣ 59፡2፣ 59፡4፣ 59፡13)፡፡*

በነዚህ ቦታዎች ላይ ፍርሃት ተብሎ የተተረጎመው በአብዱላህ ዩሱፍ አሊ የእንግሊዘኛ ትርጉም Terror ተብሎ ተቀምጧል፡፡

በሌላ ቦታ ደግሞ አላህ ሙስሊሞች ካፊሮችን ለማሸበር እንዲዘጋጁ ይነግራቸዋል፡

> *እነዚያም የካዱት ከአላህ ቅጣት ያመለጡ መኾናቸውን አያስቡ፡፡ እነሱ አያቅቱምና፡፡ ለእነሱም ከማንኛውም ኃይልና ከታጀቡ ፈረሶችም የቻላችሁትን ሁሉ በእርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከእነርሱ በቀር ያሉትን የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) **የምታሸብሩበት** ስትኾኑ አዘጋጁላቸው፡፡ ከማንኛውም ነገር በአላህ መንገድ የምትለግሱትም ምንዳው ወደናንተ በሙሉ ይሰጣል፡፡ እናንተም አትበደሉም፡፡ (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ 8፡60)*

[11] Sahih Al-Bukhari, Volume 4, book 52, Number 220
[12] Sahih Muslim, Book 004, Number 1062, 1063, 1066, 1067

## አንገት መቅላት

የሰዎችን አንገት በመቅላት መግደል እስላማዊ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ይህ ከሰብአዊነት የወጣ ተግባር በሰዑዲ አረብያ ውስጥ በህጋዊ መንገድ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ልምምድም እስልምና እስካለ ድረስ መቼም ቢሆን የሚቆም አይሆንም፤ ምክንያቱም ቁርአናዊ ትዕዛዝና የነቢዩ *ሱና* (ምሳሌነት) ነውና፡፡

> *ጌታህ ወደ መላእክቱ «እኔ (በእርዳታዬ) ከእናንተ ጋር ነኝና እነዚያን ያመኑትን አጽናኑ፡፡ በእነዚያ በካዱት ልቦች ውስጥ ፍርሃትን (Terror) በእርግጥ እጥላለሁ፡፡ ከአንገቶችም በላይ (ራሶችን) ምቱ፡፡ ከእነሱም የቅርንጫፎችን መለያልይ ሁሉ ምቱ፡፡» ሲል ያወረደውን (አስታውስ)፡፡ (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ 8፡12)፡፡*

በኒ ቁረይዟ የተሰኘ የአይሁድ ጐሣ በመሐመድ ዘመን በአረብያ ባህረ ሰላጤ ከሚገኙ ጠንካራ የአይሁድ ማህበረሰቦች መካከል አንዱ ነበር፡፡ መሐመድም ጂብሪልል ተገልጦላቸው ይህንን ማህበረሰብ **እንዲያሸብሩ** ቃል በቃል እንደነገራቸው ለተከታዮቻቸው ተናገሩ፡፡ በዚህ  የጂብሪል ትዕዛዝ መሠረት መሐመድ 3,000 ወታደሮችና 36 ፈረሰኞችን በማስከተል ድንገት በማለዳ ተከሰቱ፡፡ ከሁለት ወይም ከሦስት ሳምንታት በኋላ በኒ ቁረይዛ እጅ ሰጡ፡፡ ሴቶችና ህፃናትን ጨምሮ ቁጥራቸው ወደ 2000 ይሆን ነበር፡፡ ወንዶቹ ከሴቶችና ከህፃናት ተለይተው እጃቸው ወደ ኋላ ታስሮ እንዲቀርቡ ተደረጉ፡፡ የእዝነቱ ነቢይም ሰቆቃቸውን በመመልከት ሀሴት ያደርጉ ነበር፡፡ ከሰባት መቶ እስከ ስምንት መቶ የሚገመቱ አይሁድ ወንዶች እጆቻቸው ታስረው ወደ መዲና የገበያ ቦታ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ ሙስሊሞች ሌሊቱን ጉድጓድ ሲቆፍሩ እነዚህ አይሁዶች በጭንቀት ውስጥ ሆነው ምህረትን ይለምኑ ነበር፡፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ነቢዩ ከአጃቢዎቻቸው ጋር በመምጣት ተቀመጡ፡፡ የሞት ፍርድ የተፈረደባው አይሁዶችም ስድስት ስድስት ሆነው ወደ ጉድጓዱ እንዲቀርቡ ተደረገ፡፡ አንገታቸውን በጉድጓዱ አፋፍ ላይ አድርገው እንዲተኙ ከተደረጉ በኋላ ሁላቸውም ታረዱ፡፡ ሴቶችና ህፃናትም ለሙስሊሞች እንዲከፋፈሉ ተደረገ፡፡ ዛሬ አይኤስ ሰለባዎቹን አንድ ላይ በመሰብሰብ የጅማ እርድ (Mass Beheading) የሚፈፅመው ይህንን የመሐመድን ሱና ተከትሎ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡[13]

የሱኒ ዕውቅ ሐታች የሆነው ኢብን ከሢር የአይሁድን በጅማ መታረድ እንዲህ ሲል ገልፆታል፡ *ከዚያም የአላህ መልእክተኛ ጉድጓዶች እንዲቆፈሩ አዘዙ፤ ተቆፈሩም፡፡ እነርሱም ትከሻቸው ላይ ታስረው እንዲመጡ ከተደረገ በኋላ ታረዱ፡፡ ቁጥራቸውም ከሰባት መቶ እስከ ስምንት መቶ ይገመታል፡፡ ህፃናትና ሴቶችም ተማረኩ፤ ንብረታቸውም ተወረሰ፡፡*[14]

አሳዛኙ ነገር የበኒ ቁረይዟ አይሁዶች መሐመድ ወረዱልኝ በሚሏቸው መገለጦች አይሁዶችን በማንቋሸሻቸው ምክንያት ከማኩረፋቸው የዘለለ ሙስሊሞችን አጥቅተው የማያውቁ መሆናቸው ነው፡፡ እንዲያውም የምሽጎች ዘመቻ (The Battle of Trenches) በተሰኘ የጦርነት ውሎ ወቅት ለሙስሊሞች መሸሸግያን በማዘጋጀት ረድተው ነበር፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ ከመካ ነዋሪዎች ጋር ቢያብሩ ኖሮ ሙስሊሞችን ሙሉ በሙሉ የማጥፋት አቅም ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ያንን አላደረጉም፡፡ ነቢዩ መሐመድ ግን የእነርሱን ውለታ ወንዶቻቸውን በማረድ፣ ሴቶችና ህፃናቶቻቸውን ባርያ በማድረግና ንብረታቸውን በመዝረፍ ነበር የመለሱት፡፡

[13] Sunan Abu Dawud, 14:2665; 38:4390; Sahih Al Bukhari 4:52:280

[14] Tafsir Ibn Kathir – The Campaign against Banu Qurayzah

# ሴቶችን፣ ህፃናትንና አረጋውያንን መግደል

መሐመድ በጦርነት ወቅት ህፃናትና ሴቶች እንዳይገደሉ እንዳዘዙ የሚናገሩ ሐዲሶች ብዙ ጊዜ ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ግን የመሐመድ ትምህርት እርስ በእርሱ የሚጣረስና ወጥነት የሌለው መሆኑን ከማረጋገጥ የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡ መሐመድ ህፃናትና ሴቶች እንዳይገደሉ እንዳዘዙ ይናገራሉ የሚባልላቸውን የእስልምና ትውፊቶች ስናጠና ሴቶችና ህፃናት የሚገደሉበት አውድ መኖሩን እንደሚናገሩ ማየት እንችላለን፡፡ አንድ ሐዲስ እንዲህ ይላል፡-

> *የአላህ መልእክተኛ (ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁንና) ህፃናትን አይገድሉም ነበር ስለዚህ አል ኸዷር ስለገደለው ህፃን ያወቀውን ነገር የምታውቁ ካልሆናችሁ በስተቀር ወይንም አማኝ በመሆን በሚያድግና አማኝ ባለመሆን በሚያድግ ህፃን መካከል መለየት ካልቻላችሁ አትግደሉ፡፡ ስለዚህ አማኝ የማይሆነውን ትገድላላችሁ፤ አማኝ የሚሆነውን ደግሞ ትተዋላችሁ፡፡*[16]



ኢራቃዊ ክርስቲያን ህፃን ከመገደሉ በፊት[15] የሽብር ቡድኑ እንዲህ ዓይነቶቹን ምስሎች ሌሎችን ለማስፈራራት ይጠቀማል

በዚህ ሐዲስ መሠረት የነቢዩ መሐመድ አጠቃላይ መርህ ህፃናትን አለመግደል ቢሆንም ነገር ግን ሙስሊሞች አማኝ ባለመሆን ሊያድግ እንደሚችል የተረዱትን ህፃን መግደል እንደሚችሉ ፍቃድ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ማለት ሙስሊም ያልሆኑ ህፃናትን ከወላጆቻቸው ነጥሎ በሙስሊሞች መካከል እንዲያድጉ የማድረግ እድል ከሌለ ካፊሮች ከሆኑት ወላጆቻቸው ጋር አንድ ላይ መግደል የተፈቀደ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሙስሊም ሽብርተኞች በአዋቂዎች ስብስብ መካከል ህፃናት መኖራቸውን እያወቁ አደጋ የሚያደርሱት፡፡

በአንድ ወቅት ደግሞ መሐመድ የከሃዲያንን ወይንም ደግሞ መድብለ አማልክትን የሚያመልኩ ሰዎችን ሴቶች እና ሕፃናት መግደል ይቻል እንደሆን ተጠይቀው ነበር፡፡ እርሳቸውም ሲመልሱ “እኔ ልክ እንደ ወላጆቻቸው ነው የምቆጥራቸው” በማለት ነበር፡፡[17] በሌላ አባባል ወላጆች ከሃዲዎች ከሆኑ ልጆቻቸውን መግደል የተፈቀደ ነው ማለት ነው፡፡ የእስላም ነቢይ ያምኑ የነበሩት ይህንን ስለነበር አይኤስን የመሳሰሉት ሽብርተኛ ቡድኖች ሴቶችንና ህፃናትን መግደልን በተመለከተ የሚያምኑት ይህንኑ ነው፡፡

ሌላው ብዙ ሰዎች የማያስተውሉት እውነታ በመሐመድ መረዳት መሠረት 9 ዓመት የሞላቸው ህፃናት እንደ አዋቂዎች የሚቆጠሩ መሆናቸው ነው፡፡ ምክንያቱም በእስላማዊ ምንጮች መሠረት መሐመድ አይሻን በ6 ዓመቷ በማጨት (በአንዳንድ ምንጮች መሠረት በ7 ዓመቷ) 9 ዓመት ሲሞላት አግብተዋታልና፡፡[18] መሐመድ

---

[15] http://www.catholic.org/news/international/middle_east/story.php?id=56481 (Accessed on 5/21/2015)

[16] Sahih Muslim 4457

[17] Sahih Muslim 4322; Sahih Al Bukhari 52:256

[18] Sahih Al Bukhari 5:234; 5:236

ህፃን ለሚለው ቃል ያላቸው ትርጓሜ ከኛ ትርጓሜ ጋር ፈፅሞ የማይገናኝ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡ በኛና በእርሳቸው ትርጓሜ መካከል ቢያንስ የ8 ዓመት ልዩነት ይታያል፡፡

መሐመድ ሴቶችንም በእንቶ ፈንቶ ምክንያቶች ያስገድሉ እንደነበር በእስላማዊ ምንጮች ውስጥ ተጠቅሶ እናያለን፡-

> *ሁለት ልጃገረዶች፣ ፋርተናና ጓደኛዋ ስለ መልእክተኛው ምፀታዊ የቅኔ መዝሙር ሲዘምሩ ስለነበር እንዲገደሉ አዘዙ፡፡*[19]

መሐመድን የሚተች ቅኔ በመናገሯ ምክንያት አስማ ቢንት ማርዋን የተባለች አንዲት አስተዋይ ሴት እንዲሁ ተገድላለች፡፡ አስማ የተገደለችው ልጇን እያጠባች ሳለች እንደሆነ እስላማዊ ምንጮች ዘግበዋል፡፡[20] እንደ ዳዕሾች ሁሉ መሐመድ ለአረጋዊያንም የሚያዝን ልብ አልነበራቸውም፡፡ አቡ አፋክ በመባል የሚታወቅ እድሜው 120 እንደነበር የተነገረ በጣም የሸመገለ አይሁዳዊ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው የመሐመድን ነቢይነት በጥርጣሬ ከሚመለከቱ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ በሰይፍ ተወግቶ እንዲገደል ተደረገ፡፡[21]

አይኤስ እስልምናን የሚወክል ከሆነ ለምን ሴቶችን፣ ህፃናትንና አረጋውያንን ይገድላል የሚል መከራከርያ ለማቅረብ የሚሞክሩ ሰዎች የመሐመድን ትምህርት የማያውቁ ናቸው፡፡

## ሙስሊም ባልሆኑት ላይ ጦርነትን ማወጅና በኃይል ማስለም እንዲሁም ከእስልምና የሚወጡትን መግደል

እስልምና ነውጠኛ ከሆኑት ትምህርቶቹ የተነሳ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጎን ለጎን ተቻችሎ መኖር የሚችል ሃይማኖት አይደለም፡፡ ቁርኣንን ስንመለከት የዓለምን ታላላቅ ሃይማኖቶች በቀጥታ እየጠቀሰ ያንቋሽሻል፤ አስተምህሮታቸውንም ይተቻል፡፡ ለዚህ ነው እስልምና ባለበት ቦታ ሁሉ ሽብርና ሁከት የሚነግሰው፡፡ የእስልምና ግቡ በሌሎች እምነቶች ላይ የበላይ በመሆን ማጥፋት ነው፡፡ አይኤስ ይህንን የእስልምና ተልእኮ ከግብ ለማድረስ ቆርጦ የተነሳ በእስላማዊ መርሆች ላይ የተመሠረተ ቡድን ነው፡፡ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን ስለመዋጋትና ስለመግደል እንዲሁም አስገድዶ ስለማስለም ከሚናገሩና የአይኤስ አይዲዮሎጂ መሰረቶች ከሆኑት የቁርኣን ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

> *እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲዎች ተዋጉ፡፡ ከእናንተም ብርታትን ያግኙ፡፡ አላህም ከሚጠነቀቁት ጋር መኾኑን ዕወቁ፡፡ (የንስሐ ምዕራፍ 9፡123)*
>
> *አንተ ነቢዩ ሆይ! ከሓዲዎችንና መናፍቃንን ታገል፡፡ በእነሱም ላይ ጨክን፡፡ መኖሪያቸውም ገሀነም ናት፡፡ መመለሻይቱም ከፋች፡፡ (የንስሐ ምዕራፍ 9፡73)*
>
> *የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፡፡ ያዞዋቸውም፣ ከበቡዋቸውም፣ ለእነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ፡፡ ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡ (የንስሐ ምዕራፍ 9፡5)*

[19] Ibn Ishaq, The Life of Muhammad p. 819

[20] Ibn Ishaq, The Life of Muhammad pp. 675-676; Ibn Sa'd, Kitab al-tabaqat al-kabir pp. 30-31; Ibn Sa'd al-Baghdadi: The Book of the Major Classes Vol. 2, pp. 32

[21] (Kitab al-Maghazi, translated by Faizer R., Ismail A., & Tayob, A. K. (2011), The Life of Muhammad, pp.86-87)

*ሁከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሏቸው፡፡ ቢከለከሉም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡ (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ 8፡39)*

በሱራ 9፡5 እና ሱራ 8፡39 መሠረት ሙስሊሞች በጦርነት በማስገደድ ሰዎችን ማስለም እንደሚገባቸው ተነግሯል፡፡ ሱራ 9፡5 ላይ በተነገረው መሠረት ጦርነቱ መቀጠል ያለበት ሰዎች ሶላትን በትክክል እስኪሰግዱና ምፅዋትን (ዘካትን) እስኪሰጡ ድረስ ነው፡፡ በሌላ አባባል እስኪሰልሙ ድረስ ማለት ነው፡፡ ሱራ 8፡39 ደግሞ ጦርነቱ መቀጠል ያለበት ሁከት እስኪጠፋና ሃይማኖት ሁሉ ለአላህ እስኪሆን፣ ማለትም እስልምና ብቻ እስኪቀር ድረስ መሆኑን ይናገራል፡፡ በእስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ የሚከተለው ዘገባ ሰፍሮ እናገኛለን፡-

*ኢብን ዑመር እንዳስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፤ ሰዎች ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው እንደሌለና መሐመድም ደግሞ መልእክተኛው መሆኑን እስኪመሰክሩ ድረስ እንዲሁም ሶላትን ደንቡን ጠብቀው እስኪሰግዱ ድረስና ዘካትን እስኪሰጡ ድረስ እንድዋጋቸው (በአላህ) ታዝዣለሁ፡፡ ይህንን የሚያደርጉ ከሆነ በእስልምና ህግ ከተደነገገው በስተቀር ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን ከእኔ ይታደጋሉ፤ ድርሻቸውም በአላህ ይታሰብላቸዋል፡፡*[22]

የእስልምናው ነቢይ ሙስሊሞች ገነትን የሚያገኙት በካፊሮች ላይ ሰይፍ በመምዘዝ መሆኑን ሲያመለክቱ እንዲህ ብለዋል፡-

*ገነት በሰይፍ ጥላ ስር ናት፡፡*[23]

በሌላ ዘገባ ደግሞ ከካፊሮች ጋር ሲዋጉ ቆስለው የጠባሳ ምልክት ሳይኖራቸው አላህን የሚገናኙት ሙስሊሞች ያልበቁ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ተናግረዋል፡፡[24] በጂሃድ ላይ ሳይሳተፍና ቢያንስ ጂሃድ ላይ ለመሳተፍ ሳያስብ የሚሞት ሙስሊም ግብዝ መሆኑን መናገራቸውም ተዘግቧል፡፡[25]

እስልምና ከእምነቱ የሚወጡትን ሰዎች በመቅጣት ዙርያ ግልፅ ድንጋጌ አለው፡፡ ቅጣቱም ግድያ ሲሆን በመሐመድ የተደነገገ ነው፡፡ አይኤስም ተግባራዊ እያደረገው ይገኛል፡፡

*ነቢዩ ‹ማንኛውንም እስልምናን ለቆ የሚወጣ ሰው **ግደሉት**› ብለዋል፡፡*[26]

ሙስሊም ባልሆኑት ላይ ጦርነትን ማወጅና በኃይል ማስለም እንዲሁም ከእስልምና የሚወጡትን መግደል የእስልምና ትምህርት ነው፡፡ አይኤስም እነዚህን ትምህርቶች ወደ ተግባር በመለወጡ ከእስልምና ትምህርት የወጣ ምንም ነገር አላደረገም፡፡

## ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን መጥላት፣ መናቅ፣ ማዋረድና መርገም

እስልምና *አልወላዕ ወልበራ* ተብሎ የሚታወቅ አስተምህሮ አለው፡፡ ይህም "ለአላህ ሲሉ መውደድና መጥላት" የሚል ትንታኔን የያዘ ነው፡፡ ይህ አይኤስ በሚከተለው የሰለፊ (ወሃቢ) እስልምና አስተሳሰብ ውስጥ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ትምህርት ነው፡፡ በቁርኣን መሠረት አይሁዶችና ክርስቲያኖችን ጨምሮ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ ከየትኛውም ፍጥረት የከፉ ናቸው፡-

*እነዚያ ከመጽሐፉ ሰዎች የካዱት፣ አጋሪዎቹም በገሀነም እሳት ውስጥ ናቸው፤ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲኾኑ እነዚያ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ ክፉ ናቸው፡፡ (የግልፅ አስረጅ ምዕራፍ 98፡6)*

[22] Sahih Al-Bukhari, Vol. 1 Book 2, Number 24
[23] Sahih Bukhari, Vol. 4 Book 52, Number 73
[24] Sunan Ibn Majah, 2763
[25] Sunan An-Nasa'i, 3099
[26] Bukhari, 52:260; 83:37; 84:57; 89:271; 84:58; Abu Dawud, 4346

በአፅናፈ ዓለም ውስጥ የሚገኝ ክፉ የምትሉትን የትኛውንም ፍጥረት እስኪ አስቡ፡፡ ሙስሊም ካልሆናችሁ በቁርኣን መሠረት ከዝያ ፍጥረት ይልቅ ክፉዎች ናችሁ፡፡ ታዲያ ከፍጥረት ሁሉ የከፋ ፍጥረት ካልተጠላ ምን ሊጠላ ነው? ትክክለኛ ሙስሊሞች ያልሰለሙ ቤተሰቦቻቸውን እንኳ ወዳጅ የማያደርጉ መሆናቸውን ቁርኣን እንዲህ በማለት ይናገራል፡-

*በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፡፡ ከእርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል፡፡ (የመከራከር ምዕራፍ 58፡22)*

ሙስሊም ያልሆኑትን ቤተሰቦቹን መጥላት ያልቻለ ሰው የእስልምናን መንፈስ አልተቀበለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የእግዚአብሔር መንፈስ የፍቅር መንፈስ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ የተቀበለ ሰው እንኳንስ ቤተሰቦቹን ይቅርና ጠላቶቹን እንኳ የመውደድ አቅም አለው፡፡ በዚህ የቁርኣን ጥቅስ ውስጥ የሚታየው መንፈስ ግን የጥላቻ መንፈስ ነው፡፡ ጥላቻ የአክራሪ እስልምና መሠረት መሆኑን ለማሳየት ከዚህ የበለጠ ማስረጃ አያሻም፡፡

ቁርኣን ሙስሊሞችን ከሰው ልጆች ሁሉ ምርጦች እንደሆኑና በጎ ነገሮችን ለማዘዝና ክፉ ነገሮችን ለመከልከል ሥልጣን እንደተሰጣቸው ይናገራል፡-

*ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ታዛላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ፡፡ የመጽሐፉም ሰዎች ባመኑ ኖሮ ለነርሱ የተሻለ በኾነ ነበር፡፡ ከነርሱ አማኞች አሉ፡፡ አብዛኞቻቸው ግን አመጸኞች ናቸው፡፡ (የዒምራን ቤተሰብ ምዕራፍ 3፡110)*

ይህ የቁርኣን ቃል ፅንፈኛ ሙስሊሞች የበላይነትን ለመቆናጠጥ እንዲታገሉና በበታችነት ስሜት በሽታ (Inferiority Complex) የተመቱ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የበላዮች እንደሆኑ በማሰብ ሌሎችን ይንቃሉ ነገር ግን ደግሞ በብዙ ነገር ኋላ ቀሮች የመሆናቸው እውነታ ይታገላቸዋል፤ ስለዚህ በምናባቸውና በእውነታ መካከል ይማስናሉ፡፡ ይህ ደግሞ የተናጋና ነውጠኛ ስነልቦና እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

መሐመድ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን ማዋረድ እንደሚገባቸው አስተምረዋል፡፡ በመንገድ ላይ እንኳ ሲመጡባቸው ሰላም እንዳይሏቸውና እንዲገፈትሯቸው አዘዋል፡- *ነቢዩ (የአላህ ሰላምና በረከት በእሳቸው ላይ ይሁንና) እንዲህ ብለዋል ‹አይሁዶችን ወይንም ክርስቲያኖችን ቀድማችሁ ሰላም አትበሉ፡፡ በመንገድ ላይ ቢመጡባችሁ ወደ ጠባቡ የመንገድ ጠርዝ ግፏቸው፡፡›*[27]

እንዲሁም በቁርኣን ውስጥ የእርግማንን ቃላት በክርስቲያኖችና በአይሁዶች ላይ ሲናገሩ እንመለከታለን፡-

*አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች፡፡ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፡፡ ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፡፡ የእነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፡፡ አላህ ያጥፋቸው፡፡ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ! (የንስሐ ምዕራፍ 9፡30)*

መሐመድ ሕይወታቸው ከማለፉ በፊት የተናገሩት የመጨረሻው ንግግራቸው አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን መርገም እንደነበር እስላማዊ ትውፊቶች ይናገራሉ፡:

*አይሻና አብዱላህ እንደዘገቡት ፡ የአላህ ምልእክተና (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁንና) የመጨረሻ እስትንፋሳቸውን ሊተነፍሱ በነበሩበት ጊዜ ፊታቸውን በአንሶላው ሸፈኑ፤ ትንሽ ከተረጋጉ በኋላ*

[27] Sahih Muslim, 2167; Sahih Ai-Bukhari Book 25, Number 5389 በተጨማሪም ኢማም አን-ነወዊ፣ ሪያዱ ሷሊሒን፣ ከሐዲስ ቁጥር 811-1896፣ ቅፅ 2፣ ትርጉም በሐሰን ታጁ፣ ገፅ 42 ይመልከቱ

*ፊታቸውን ገለጡና በዚያ ሁኔታ እያሉ እንዲህ አሉ ‹የሐዋርያቶቻቸውን መቃብሮች እንደ ፀሎት ቦታ በመጠቀማቸው በአይሁዶችና በክርስቲያኖች ላይ እርግማን ይሁን፡፡› (ተከታዮቻቸውንም) (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) የሚያደርጉትን ነገር እንዳያደርጉ አስጠንቅቀዋል፡፡*[28]

ታድያ ዳዕሾች ሙስሊም ያልሆኑትን ሰዎች በመጥላታቸው፣ በመናቃቸው፣ በማዋረዳቸውና በመርገማቸው ከእስልምና የወጣ ምን ነገር አደረጉ? ምንም!

## ሴቶችን የወሲብ ባርያ ማድረግና ህፃናትን መድፈር

አይኤስን የመሳሰሉ አረመኔ ቡድኖች ከሚታወቁባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ሴቶችን የወሲብ ባርያ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በመሐመድ ሱና (ምሳሌነት) የተረጋገጠ ቁርአናዊ ትምህርት ነው፡፡ ልክ እንደዛሬዎቹ ዳዕሾች መሐመድ የወሲብ ባርያዎች ነበሯቸው፡፡ ይህ ደግሞ በትውፊቶች ብቻ ሳይሆን የአምላክ ዘላለማዊ ቃል እንደሆነ በተነገረለት በቁርአንም ውስጥ ተጽፎ የሚገኝ ነው፡-

*አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር የተሰደዱትን የአጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜዎችህንም ሴቶች ልጆች (ማግባትን)*[30] *ለአንተ ፈቅደንልሃል፡፡ የአመነችንም ሴት ነፍሷን (ራሷን) ለነቢዩ ብትሰጥ ነቢዩ ሊያገባት የፈለገ እንደ ኾነ ከምእምናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትኾን (ፈቀድንልህ)፡፡ በእነርሱ (በምእምናን) ላይ በሚስቶቻቸውና እጆቻቸው በጨበጧቸው (ባሮች ነገር) ግዴታ ያደረግንባቸውን በእርግጥ ዐውቀናል፡፡ ባንተ ላይ ችግር እንዳይኖር (ያለፉትን ፈቀድንልህ)፡፡ አላህም መሓሪ አዛኝ ነው፡፡ (የአሕዛብ ምዕራፍ 33፡50)*

በዚህ የሥጋ ዘመዶቻቸውን ባካተተ ዝርዝር ውስጥ "አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች" የሚለው በጦርነት ወቅት ተማርከው ባርያዎች የተደረጉ ሴቶችን ያመለክታል፡፡ የመሐመድ ህፃን ሚስት አይሻ በአንድ ወቅት "አላህ የርሶን ምኞት ለማርካት ተጣድፏል" በማለት ነቢዩን በነገር እንደሸነቆጠቻቸው በእስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ ተዘግቧል፡፡[31] መሐመድ የግል ፍላጎታቸውን ለማርካት ለሥጋዊ ጥቅማቸው ሲሉ ይህንን መገለጥ እንደተናገሩት ግልፅ ነው፡፡ እውነተኛው አምላክ የአንድን ግለሰብ ፍላጎት ለማሟላት በዘላለማዊ መጽሐፉ ውስጥ ይህንን መገለጥ ጽፎ አስቀምጧል ብሎ ማመን ጭፍንነት ነው፡፡ የወሲብ ባርያዎችን መያዝ ለመሐመድ ብቻ ሳይሆን ለሙስሊም ወንዶች ሁሉ የተፈቀደ መሆኑን ቁርአን በሚከሉት ቦታዎች ላይ ይናገራል፡-



የኢራቅ ክርስቲያን ሴቶች እንደ ሙስሊም እንዲለብሱ ተደርገው በሰንሰለት በመታሰር ለወሲብ ባርነት ሲወሰዱ[29]

---

[28] Sahih Muslim 1082; Sahih Al-Bukhari 2:23:472

[29] http://www.christianpost.com/news/un-report-on-isis-24000-killed-injured-by-islamic-state-children-used-as-soldiers-women-sold-as-sex-slaves-127761/ (Accessed on 20/5/2015)

[30] በጥቅሱ ውስጥ በቅንፍ የተቀመጠው "ማግባት" የሚለው ቃል በተርጓሚዎቹ የተጨመረ እንጂ በዋናው አረብኛ ውስጥ እንደማይገኝ ልብ ይሏል፡፡ አረብኛው የተዘረዘሩት ሴቶች ለመሐመድ የወሲብ መጠቀምያ መሆን እንደሚችሉ ነው የሚናገረው፡፡

[31] Sahih Al-Bukhari, 60:311

*እነዚያም እነርሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት (አገኙ)፡፡ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር፡፡ እነርሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና፡፡ (የምዕመናን ምዕራፍ 23፡5-6)*

*ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፡፡ ከዚሃችሁም (ከተከለከሉት) ወዲያ ጥብቆች ኾናችሁ ዝሙተኞች ሳትኾኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለእናንተ ተፈቀደ፡፡ ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲኾን ስጧቸው፡፡ ከመወሰንም በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በእናንተ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና፡፡ (የሴቶች ምዕራፍ 4፡24)*

ሱራ 4፡24 ላይ በተጻፈው መሠረት ሙስሊም ወንዶች ባል ካላቸው ነፃ ሴቶች ጋር ወሲብ መፈፀም የማይፈቀድላቸው ሲሆን ነገር ግን በጦርነት ላይ የማረኳቸውን ሴቶች ባሎቻቸው በሕይወት ቢኖሩ እንኳ ለወሲብ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ከጋብቻ ውጪ በሆነ ሁኔታ ሴቶችን ለወሲብ ባርነት መጠቀም የተፈቀደ መሆኑን እንደሚያሳዩ ሙስሊም ሐታቾች ይስማማሉ፡፡ መሐመድና ወታደሮቻቸው ባሎችን በመግደል ሚስቶችን ለወሲብ ይጠቀሙ እንደነበር በብዙ እስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ ተዘግቦ እናገኛለን፡፡[32] አይኤስ ይህንን በመሐመድና በመጀመርያዎቹ ሙስሊሞች ሲተገበር የነበረ ቁርኣናዊ ትምህርት እየተገበረ ይገኛል፡፡ ከዚህም የተነሳ ብዙ የያዚዲና የክርስቲያን ሴቶች በማይነገር ሰቆቃ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ብዙ ፖለቲከኞችና የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾች በዚህ ድርጊት ቁጣቸውንና ተቃውሟቸውን ቢገልፁም ነገር ግን እስላማዊ መሠረት እንዳላው የሚያውቁ አይመስሉም፤ ወይንም ደግሞ እስላማዊ መሠረት እንዳለው ለማመን አይፈልጉም፡፡

ሌላው አይኤስ ከሚታወቅባቸው ኢ-ሰብኣዊ ድርጊቶች መካከል አንዱ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱትን ሴቶች የወሲብ መጠቀምያ ማድረግ ነው፡፡ መሐመድ አይሻን በ6 ዓመቷ በማጨት 9 ዓመት ሲሞላት በማግባት ለዳዕሾች ጥሩ ምሳሌ ሆነዋቸዋል፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑ እስላማዊ ትውፊቶችን ቀደም ሲል ጠቅሰናል፡፡ በቁርኣን ውስጥ ገና የወር አበባን ያላዩ (ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ) ሴቶችን መፍታት ስለሚቻልበት ሁኔታ መመርያ የሚሰጥ አንድ ጥቅስ ይገኛል፡-

*እኒያም ከሴቶቻቸው ከአደፍ ያቋረጡት (በዒዳቸው ሕግ) ብትጠራጠሩ ዒዳቸው ሦስት ወር ነው፡፡ እኒያም ገና አደፍን ያላዩት (ዒዳቸው እንደዚሁ ነው)፡፡ የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው እርጉዛቸውን መውለድ ነው፡፡ አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለርሱ መግራትን ያደርግለታል፡፡ (የፍች ምዕራፍ 65፡4)*

ይህንን ጥቅስ ግልፅ ለማድረግ ያህል አንድ ሙስሊም ወንድ አንዲትን የወር አበባዋ የተቋረጠ ሴት ለመፍታት ቢፈልግ ለሦስት ወር ያህል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይፈፅም ይቆያል፡፡ ለአቅመ ሔዋን ባለመድረሷ ምክንያት የወር አበባ ያላየችን ሴት ለመፍታት ቢፈልግ እንዲሁ ሦስት ወር ያህል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይፈፅም ይጠብቃል፡፡ ይህ የቁርኣን ሐታቾች ሁሉ የሚስማሙበት እስላማዊ መመርያ ነው፡፡ ሰይድ አቡል ዓላ ማውዱዲ የተሰኙ ፓኪስታናዊ ሙስሊም ሊቅ ይህንን ጥቅስ በተመለከተ እንዲህ ይላሉ፡-

*ገና አደፍን ያላዩትን (የወር አበባ ያላዩትን) መፍታት የሚቻልበትን መመርያ የሚሰጠው ይህ የቁርኣን ጥቅስ እንዲህ አይነት ሴቶችንም ማግባት እንደሚቻል በግልፅ የሚያሳይ ነው፤ በመሆኑም ቁርኣን ያፀደቀውን ይህንን ተግባር ማንም የመከልከል መብት የለውም፡፡*[33]

[32] Sahih Al-Bukhari, 62:137; Bukhari 34:432; Abu Dawud 2150

[33] Sayid abul A'La maududi, The meaning of the Qur'an Vol. 5 pp. 599 & 617

ማውዱዲ በሙስሊሙ ዓለም እጅግ የተከበሩ ዕውቅ የቁርኣን ተንታኝ ናቸው።

መሐመድ በዳዴ የሚሄዱትን አራስ ህፃናት እንኳ ሳይቀር ለጋብቻ ይመኙ እንደነበር በእስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ ማንበብ በእጅጉ አስደንጋጭ ነው።

> *የአባስ ልጅ ኡም ሐቢባ ጡት በመጥባት እድሜ ላይ በነበረች ጊዜ በፊታቸው በዳዴ ስትሄድ መሐመድ ተመልክተዋት እንዲህ አሉ፡ ‹እኔ በሕይወት እያለሁ የምታድግ ከሆነ አገባታለሁ።›*[34]

አድጎ ለጋብቻ መብቃት ማለት በመሐመድ እምነት መሠረት 9 ዓመት መሙላት ነው። ይህ ደግሞ በፀሐይ ዓመት ሳይሆን አረቦች በሚጠቀሙት የጨረቃ ዓመት ነው። የጨረቃ ዓመት እኛ ከምንጠቀመው የፀሐይ ዓመት እንደሚያጥር ልብ ይሏል።

ዳዕሾች ህፃናትን ለወሲብ መጠቀማቸው በመሐመድ ሱና ላይ የተመሠረተ መሆኑ ግልፅ ነው። ስለዚህ ይህ የአይኤስ ተግባር እስላማዊ ነው።

## ሰዎችን ኢ-ሰብኣዊ በሆነ ሁኔታ ማሰቃየትና መግደል

ዳዕሾች ፍፁም አውሬያዊ በሆነ ሁኔታ ሰዎችን ሲያሰቃዩና ሲገድሉ ማየት የተለመደ ሆኗል። የጭካኔያቸውን ደረጃ ስንመለከት ሰይጣን እንኳን ይህን ያህል በሰው ልጆች ላይ መጨከኑ ያጠራጥራል። ብዙ ሰዎችም ይህንን በቃላት ሊገለፅ የማይችል አረመኔያዊ ተግባራቸውን በማየት እስልምና እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ሊፈቅድ እንደማይችል ይገምታሉ። ወገኖቼ የእስልምናን ምንጮች ብታገላብጡ ዳዕሾች ነቢዩ መሐመድና የመጀመርያዎቹ ሙስሊሞች ሲፈፅሙ ከነበሩት የተለየ ምንም ነገር እንደላደረጉ ታረጋግጣላችሁ። እስኪ ቁርኣን ካፊሮችን ስለማሰቃየት ምን እንደሚል እንመልከት፡-

> *የእነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር መባረር ነው። ይህ በነሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው። በመጨረሻይቱም ለእነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው። (የማእድ ምዕራፍ 5፡33)*

ቀደም ሲል እንደተገለፀው አላህንና መልክተኛውን መዋጋት ማለት በእስላማዊ አተረጓጎም መሠረት ማንኛውንም ቁርኣንንና እስላማዊ ህግጋትን መፃረር እንዲሁም የመሐመድን ነቢይነት አለመቀበል ማለት ነው። በምድር ላይ ማጥፋት ደግሞ ለሙስሊም ማህበረሰብ እንቅፋት የሚሆን ማንኛውንም ነገር ማድረግን ያመለክታል። ወንጌልን መስበክን ጨምሮ ከእስልምና ንፅረተ ዓለም ውጪ የሚገኝን የትኛውንም ትምህርት ማስተማር በሸሪኣ ህግ መሠረት ለነዚህ ቅጣቶች ይዳርጋል።

> *የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ እነዚያም ከእርሱ ጋር ያሉት (ወዳጆቹ) በከሓዲዎቹ ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው አዛኞች ናቸው። (አገር የመከፈት ምዕራፍ 48፡29)*

ይህ ጥቅስ በአረብኛ ሲነበብ መሐመድና ተከታዮቻቸው በካፊሮች ላይ ምህረት የለሽ ጨካኞች (Ruthless) እና እርስ በእርሳቸው ደግሞ የሚተዛዘኑ መሆናቸውን የሚናገር ነው። ይህ የመሐመድና የተከታዮቻቸው መለያ ነው። ሌላውን በጭካኔ ማረድ፣ እርስ በርስ ግን መተዛዘን። በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ ደግሞ በካፊሮች ላይ መጨከን የአላህ ትእዛዝ መሆኑን እናያለን፡-

> *አንተ ነቢዩ ሆይ! ከሓዲዎችንና መናፍቃንን ታገል። በእነሱም ላይ ጨክን። መኖሪያቸውም ገሀነም ናት። መመለሻይቱም ከፋች። (የንስሐ ምዕራፍ 9፡73)*

---

[34] Musnad Ahmed, Number 25636

በአንድ ወቅት የተወሰኑ ሰዎች ወደ መሐመድ በመምጣት እስልምናን ተቀበሉ፡፡ መሐመድም በደህና አስተናገዷቸው፡፡ የመዲና የአየር ሁኔታ ስላልተስማማቸው ወደ ግመል መንጋ በመሄድ ወተታቸውንና ሽንታቸውን ለመድኃኒትነት እንዲጠጡ አዘዟቸው፡፡ ሰዎቹ ከተሻላቸው በኋላ የመሐመድን እረኛ በመግደል ግመሎቹን ወስደው ሄዱ፡፡ መሐመድም ወታደሮቹን በመላክ ተከታትለው ይዘዋቸው እንዲመጡ አደረጉ፡፡ ከዝያም ዓይን ስለ ዓይን ጥርስ ስለ ጥርስ በሚለው ትእዛዝ መሠረት ሳይሆን ለመስማት በሚዘገንን ሁኔታ ቀጧቸው፡፡ ቡኻሪ የተሰኙት የትውፊት ዘጋቢ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡-

*(ነቢዩ) እጆቻቸውና እግሮቻቸው እንዲቆረጡ አዘዙ፤ ተቆረጡም፡፡ ዓይኖቻቸውም በጋለ ብረት ተጠብሶ እንዲጠፉ ተደረገ፡፡ ከዝያም እስኪሞቱ ድረስ በአል ሀራ (ፀሐያማ የሆነ የመዲና ደረቅ ቦታ) ላይ ተጣሉ፡፡ ውኃ በጠየቁ ጊዜ ምንም ውኃ አልተሰጣቸውም ነበር፡፡*[35]

በሚከተለው ሐዲስ መሠረት ነቢዩ መሐመድ ለገንዘብ ብለው ሰዎችን ያሰቃዩ እንደነበር እናያለን፡፡ በሐዲሱ ውስጥ የተጠቀሰው ሰው በኸይበር የሚገኙ አይሁዶች መሪ የነበረ ወጣትና አዲስ ሙሽራ ነበር፡፡ መሐመድ ካስገደሉት በኋላ መልከመልካም የ17 ዓመት ወጣት የነበረችውን ሚስቱ ሰፊያን ለራሳቸው ወስደዋል፡፡ ሐዲሱ እንዲህ ይነበባል፡-

*ነቢዩ ኪናና የተባለውን ሰው በተመለከ ለዙባይር እንዲህ የሚል ትእዛዝ ሰጡ ‹በውስጡ የደበቀውን ሁሉ እስኪያወጣ ድረስ አሰቃየው፡፡› ስለዚህ ዙባይር ኪናና ለሞት እስኪቃረብ ድረስ ደረቱ ላይ እሳት አስቀመጠበት፡፡ ከዚያም ነቢዩ ለመሰለማህ አሳልፈው ሰጡት፡፡ እርሱም አረደው፡፡*[36]

መሐመድ ሰዎች በእሳት እንዳይቃጠሉ እንደከለከሉ የሚናገሩ ሐዲሶች አሉ ነገር ግን ደግሞ ሰዎች በእሳት እንዲቃጠሉ ያዘዙባቸው ቦታዎችም አሉ፡፡[37] ዳዕሾች ዮርዳኖሳዊውን የአውሮፕላን አብራሪ ያቃጠሉት ዓይን ስለ ዓይን ጥርስ ስለ ጥርስ በሚለው መርህ መሠረት እንደሆነ የተናገሩ ሲሆን እነዚህ እስላማዊ ምንጮችም ተጨማሪ ድጋፍ ይሰጡዋቸዋል፡፡ ሌላው እጅግ አሰቃቂና ለመስማት የሚዘገንን የነቢዩ መሐመድና የተከታዮቻቸው የጭካኔ ታሪክ አል-ጦበሪ እና ኢብን ኢስሐቅ በጻፏቸው የመሐመድ ታሪኮች ውስጥ ይገኛል፡-

*የ80 ዓመት ዕድሜ ባለጠጋ የሆነች ትክክለኛ ስሟ ፋጢማ ቢንት ሩቢያዐ የተሰኘ ኡም ቀረፌ የምትባል ሴት ነበረች፡፡ መሐመድን የሚተች ግጥም በማዘጋጀትም ትደግም ነበር፡፡ 13 ወንዶች ልጆች የነበሯት ሲሆን ሁሉም ጎልማሶችና የአይሁድ ጎሳ መሪዎች ነበሩ፡፡ በዘይድ የሚመራ አጥቂ ቡድን በረመዳን ወቅት በኡም ላይ ዘመተ፡፡ በዚያን ጊዜ ኡም አሳቃቂ አሟሟት ሞተች፡፡ ዘይድ እግሮቿን በገመድ አድርጎ በሁለት ግመሎች መካከል አሰራት፡፡ በተቃራኒ አቅጣጫዎችም እንዲሄዱ አደረገ፤ እርሷም ለሁለት ተሰነጠቀች፡፡*[38]

---

[35] Sahih Al-Bukhari 7:71:623; 5:59:505; 1:4:234; 4:52:261; Sahih Muslim 16:4131; 16:4130; 16:4132; 16:4134; Abu Dawud 38:4356; 36:4357

[36] Al-Tabari, Vol. 8, p. 122

[37] Sahih Al-Bukhari 11:626; Ishaq's Sirat Rasul Allah, 1955, p. 316

[38] Al-Tabari, Vol. 8, p.96; Ishaq's Sirat Rasul Allah, 1955, pp. 664-665

❸

# አይኤስ እስልምናን የሚወክል ከሆነ ስለ ምን ሙስሊሞችንም ጭምር ይጎዳል?

ይህ ጥያቄ ብዙ ሰዎች የአይኤስን እስላማዊነት እንዲጠራጠሩ ምክንያት የሆናቸው ይመስላል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን ሰፋ አድርገን የተመለከትን እንደሆነ ሁሉም ነገር ይገባናል፡፡ የሚከተሉትን አራት ነጥቦች በአንክሮ ካጤናችሁ በኋላ ይህ የሽብር ቡድን ከእስልምና ውጪ የሚገኙትን ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን ሙስሊሞችንም ጭምር የጥቃቱ ዒላማ ማድረጉ እንዲያውም እስላማዊ ቡድን መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ትገነዘባላችሁ፡፡

1. አይኤስ በሙስሊሞች ላይ ጉዳት ማድረሱ እስላማዊ ተግባር የሚሆንበት የመጀመርያው ምክንያት በቁርኣን መሠረት ክርስቲያኖችና አይሁዶችን የሚወዳጁ ሙስሊሞች ልክ እንደእነርሱ የሚቆጠሩ በመሆናቸው ነው፡- *እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ፡፡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱ ነው፡፡ አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም፡፡ (የማእድ ምዕራፍ 5፡51)*

   ካፊሮችን የሚወዳጁ ሙስሊሞች ወደ ገሃነም ይወርዳሉ፡- *ከእነሱ ብዙዎቹን እነዚያን የካዱትን ሲወዳጁ ታያለህ፡፡ በእነሱ ላይ አላህ የተቆጣባቸው በመኾኑ ለእነርሱ ነፍሶቻቸው ያስቀደሙት ሥራ በጣም ከፋ፡፡ እነሱም በቅጣት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡ (የማእድ ምዕራፍ 5፡80)*

ካፊር የቤተሰብ አባላቶቻቸውን እንኳን ቢሆን የሚወዳጁ ሙስሊሞች በደለኞች ናቸው፡- *እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አባቶቻችሁና ወንድሞቻችሁ ክህደትን ከእምነት አብልጠው ቢወዱ ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙዋቸው፡፡ ከእናንተም ውስጥ ወዳጅ የሚያደርጋቸው እነዚያ እነሱ በዳዮች ናቸው፡፡ (የንስሐ ምዕራፍ 9፡23)*

አቡ ዳውድ እንዲህ ብሏል፡- *ከሙሽሪክ (ከአላህ ውጪ ሌላ ነገር የሚያመልክ ሰው) ጋር የሚተባበርና አብሮት የሚኖር ሰው ልክ እንደ እርሱ ነው፡፡*[39]

ተመሳሳይ ዘገባዎችን በሌሎች ሐዲሳት ውስጥም እናገኛለን፡፡ ኢብን ከሢር እና ኢብን ተይሚያን ጨምሮ ብዙ ሙስሊም ሊቃውንትም ይህንኑ ሐሳብ ያፀናሉ፡፡ ስለዚህ አይኤስን የመሳሰሉት እስላማዊ ቡድኖች ሙስሊሞችን ሲገድሉ በዚህ መነሻ ነው፡፡ ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር፣ በተለይም ደግሞ ከምዕራባውያን ክርስቲያኖችና ከአይሁዶች ጋር የሚወዳጁ ሙስሊሞች ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ (ኡማ) አደገኞች እንደሆኑ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሰዎች መግደል ሙስሊሙን ማሕበረሰብ ከጉዳት መከላከል ነው የሚል አመክንዮ አላቸው፡፡ አላህ ደግሞ በቁርኣኑ ውስጥ ካፊሮችን የሚወዳጁ ሙስሊሞች እውነተኛ ሙስሊሞች አለመሆናቸውንና ልክ እንደካፊሮች መሆናቸውን በመናገር እርምጃውን ያፀድቀዋል፡፡ ካፊሮች መገደል ካለባቸው እነዚህ ሙስሊሞችም መገደል አለባቸው፡፡ ስለዚህ አይኤስ በቁርኣን ያልተደገፈና እስላማዊ ያልሆነ ነገር እየፈፀመ አይደለም፡፡

2. ሌላው ደግሞ በእስልምና ውስጥ ብዙ አንጃዎች የመኖራቸው ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ አንጃዎች እርስ በርሳቸው የሚወነጃጀሉና አንዳቸው ሌላቸውን እንደ ካፊር የሚቆጥሩ ናቸው፡፡ በተለይም የሺአና የሱኒ ሙስሊሞች በፖለቲካዊ ጥቅም ከመጋጨታቸውም በላይ አንዳቸው ሌላቸውን እንደ እውነተኛ ሙስሊም አይቆጥሩም፡፡ ነገር ግን ሙስሊሞች የውስጥ ሽኩቻዎቻቸውን ለውጪው ዓለም በመግለጥ እስልምና

[39] Sunan Abu Dawud: 2787

እርስ በርሱ የተከፋፈለ መሆኑን ማሳወቅ ስለማይፈልጉ በእስላማዊ አንጃዎች መካከል ያለውን የጥላቻ ጥልቀት ለማወቅ ቀረብ ብሎ መመልከት ያሻል፡፡

3. እነዚህ ቡድኖች ሙስሊሞችን የሚገድሉበት ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ከራሱ ከእስልምና ተፈጥሮ የሚመነጭ ነው፡፡ እስልምና ከእግዚአብሔር የሆነ ሃይማኖት አይደለም፡፡ መሰረቱም ጥላቻና ትዕቢት ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የሌለበት ዓለም ስለሆነ የሁከት ዓለም ነው፡፡ ሙስሊሞች የውጪ ጠላት ሲመጣባቸው ተባብረው የጋራ ጠላታቸውን ለመዋጋት ይሞክራሉ፡፡ የውጪው አየር ሰላም ሲሆንም ደግሞ ሥራ አይፈቱም፡፡ እርስ በርሳቸው ይዋጋሉ፡፡ የእስልምናን የመጀመርያዎቹን ዘመናት ስንመለከት መሪዎቹ እርስ በርሳቸው በመገዳደል ነበር ሥልጣን ሲነጣጠቁ የነበሩት፡፡ ከመሐመድ ጋር የነበሩት የመሐመድ ወዳጆች ከእርሳቸው ህልፈት በኋላ በመካከላቸው የነበረው አንድነት ተናግቶ ነበር፡፡ ዑመር በጠላታቸው ተገደሉ፡፡ ከዑመር በኋላ ስልጣን የተረከቡት ኡሥማን እንዲሁ ተገደሉ፡፡ ሦስተኛው ኸሊፋ አሊም እንደዚሁ ተገደሉ፡፡ ይህም እስከ ዛሬ ድረስ በሺአና በሱኒ መካከል ለተፈጠረው የከረረ ክፍፍልና ጥላቻ መንገድ ጠረገ፡፡ የአሊ ልጅ ሁሴንም እንደዚሁ ተገደሉ፡፡ ይህም ክፍፍሉን እስከ ወድያኛው አፀናው፡፡ ስለዚህ እስልምና መሰረቱ ጥላቻ ስለሆነ ሙስሊሞች ከሌላው ወገን ጋርም ሆነ እርስ በርሳቸው ተቻችለው መኖር ይሳናቸዋል፡፡

4. እነዚህ ሰዎች ሙስሊሞችን ለምን ይገድላሉ ለሚለው ጥያቄ ሊጠቀስ የሚችል አራተኛው ምክንያት እስልምና በሚከተለው ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እስልምና የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው ዓይነት ፍልስፍናን የሚከተል ሃይማኖት ነው፡፡ ይህም ማለት ውጤቱ አካሄድህን ያፀድቃል (The end justifies the means) በማለት ያምናል ማለት ነው፡፡ ሙስሊሞች የሚያደርጉት ነገር መልካም ውጤትን የሚያስገኝና እስልምናን የሚጠቅም ከሆነ ማንኛውንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ሙስሊም ማሕበረሰቦችን ማዋከብ በረጅም ጊዜ እስላማዊ እቅድ ጠቃሚ የሆነን ውጤት የሚያስገኝ ከሆነ ያደርጉታል፡፡ ዳዕሾች ሙስሊሞችን ማወከና አስጨንቆ ከአገር እንዲሰደዱ ማድረግ በሁለት መልኩ እስልምናን የሚጠቅም እንደሆነ ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ የመጀመርያው ለክርስቲያኖች ከለላን የሚሰጡ መንግሥታዊ ተቋማትንና ማህበረሰባዊ አደረጃጀቶችን በማፈራረስ አካባቢውን ከክርስቲያኖች ማፅዳት ማስቻሉ ነው፡፡ ይህም ደግሞ በተሳካ ሁኔታ እየተፈፀመ ይገኛል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሙስሊሞች በብዛት መካከለኛውን ምስራቅ ለቀው እንዲወጡ በማድረግ ሙስሊም ወዳልሆኑ አገራት ተሰደው እንዲሰፍሩና በስብከትና በጦርነት ማግኘት ያልተቻለውን ውጤት በዚህ መልኩ ለማግኘት የተጠነሰሰ ሴራ የመኖሩ ሁኔታ ከፍተኛ ነው፡፡ ስደት እስልምና ከሚስፋፋባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡[40] በአሁኑ ወቅት ከሦርያና ከሊብያ የሚጎርፉት ሙስሊም ስደተኞች የአውሮፓን ወደቦች እያጨናነቁ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ስደተኞች የእግር ማሳረፍያ ቦታ ካገኙ በኋላ እስላማዊ የሆነን ማሕበረሰብ ይመሰርታሉ፡፡ እስላማዊውን ተልዕኮ በሚገባ መፈፀም ይችሉ ዘንድ የሚያስተምሯቸውና የሚያደራጇቸው ለዚሁ ዓላማ የተሰለፉ ስልጡኖች ተዘጋጅተው ስለሚጠብቋቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፅዕኖን ማሳረፍ ወደሚችሉ ማሕበረሰቦች ያድጋሉ፡፡ እንዲሁ ከላይ ሲታይ ሙስሊሙን ማሕበረሰብ የሚጎዳ የሚመስለውም ነገር (ሁከትና ስደት) በዚህ መልኩ የእስልምናን የረጅም ጊዜ ዕቅድ ለማሳካት መንገድ ከፋች ይሆናል ማለት ነው፡፡ ልብ ያለው ልብ ይበል!

ከላይ የተቀመጡትን አራት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ያስገባ ሰው አይኤስ ሙስሊሞችን በመግደሉና በማሳደዱ እስላማዊ እንዳልሆነ ሊደመድም አይ

---

[40] በእስልምና መስፋፋት ውስጥ ስደት ምን ዓይነት ሚና እንደሚጫወት ለማወቅ "Al-Hijra, Islamic Doctrine of Migration, Accepting Freedom or Imposing Islam" በሚል ርዕስ በዶ/ር ሳም ሶሎሞንና በኤልያስ አልመቅዲሲ የተጻፈውን ዓይን ከፋች መጽሐፍ አግኝታችሁ ታነቡ ዘንድ አበረታታችኋለሁ፡፡

4

## ሙስሊሞች የአይኤስን ተግባር የሚኮንኑትና እስልምናን እንደማይወክል የሚናገሩት ለምንድነው?

ሙስሊሞች ሁሉ አንድ ዓይነት አይደሉም፡፡ እስልምና ሽብርን እንደሚያበረታታ የሚያውቁ ነገር ግን ሰብኣዊነት የሚሰማቸውና እንዲህ ዓይነቱን ነውጠኛ ትምህርት የማይቀበሉ ከሙስሊም ማሕበረሰብ ጋር በጥልቀት ስለተቆራኙ ብቻ እስልምናን ለቀው መውጣት ያልቻሉ ሙስሊሞች አሉ፡፡ እነዚህ ሙስሊሞች ተራማጅ አመለካከት ያላቸውና ነውጠኛ የሆኑት የእስልምና ትምህርቶች በተሃድሶ መወገድ እንዳለባቸው የሚያምኑ ናቸው፡፡ ነገር ግን እስልምና እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ሊታደስ የሚችል እምነት አይደለም፡፡ ይልቁኑ የእስልምና ተሃድሶ ጨለማዊ ወደ ሆነው ወደ መሐመድ ዘመን መመለስ መሆኑን እየተመለከትን ነው፡፡

ሌሎች ሙስሊሞች ደግሞ እነዚህ ነውጠኛ እስላማዊ ትምህርቶች ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን የጦርነት ታሪኮች ሁሉ በዚያ ዘመንና በዚያ ቦታ ብቻ የተወሰኑ እንደሆኑ ስለሚያምኑ የሽብር ድርጊቶችን ይቃወማሉ፡፡ ነገር ግን ቁርኣንንና እስላማዊ ትውፊቶችን በዚህ መልኩ መተርጎም የማይቻልባቸው የሥነ-ፍታቴና የታሪክ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህ ትምህርቶች የራሳቸው የሆነ ታሪካዊ አውድ ቢኖራቸውም ነገር ግን በየትኛውም ዘመን ለሚኖሩ ሙስሊሞች የሚያገለግሉ መመርያዎች መሆናቸውን ቁርኣንን በመተንተን ረገድ ሥልጣንና ዕውቀቱ ያላቸው ሙስሊም ሐታቾች ይስማማሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት አተረጓጎምም ከትክክለኛው እስልምና ውጪ ነው፡፡ በዚህ መነሻ ሰላምን የሚሰብኩ ሙስሊሞች እጣ ፈንታቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ በአንዳንድ የአገራችን ሙስሊም ሊቃውንት ላይ የደረሰውን ማየት በቂ ነው፡፡

ሌላው የአይኤስን ተግባር የሚቃወሙ እስልምና ምን እንደሚያስተምር የማያውቁና በነውጠኛ ትምህርቶቹ ያልተበከሉ ሙስሊሞች መኖራቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡ የአገራችን አብዛኞቹ ሙስሊሞች በኢትዮጵያዊነት ሥነ ምግባር ያደጉና ቁርኣንን በጥልቀት የማያውቁ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው ሰለፎች (ወሃቢዮች) የኢትዮጵያን ሙስሊሞች ከእንደገና የማስለም ዘመቻ በመክፈት እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊምና አረባዊ ሙስሊም እየተወያዩ ሳሉ ኢትዮጵያዊው ሙስሊም እኛ እስልምናን በሰይፍ ተገደን ሳይሆን በውድ ነው የተቀበልነው በማለት በኩራት ሲናገር አረባዊው ሙስሊም መልሶ እናንተ እስልምናን ያለሰይፍ እንደተቀበላችሁት ሁሉ ለቃችሁት ስትወጡም ያለሰይፍ ነው አለው ይባላል፡፡ አሁን እየተደረገ ያለው በአንፃራዊነት ሰላማውያን የሆኑትን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሰይፍ ወደሚያምኑ የሰለፊ (ወሃቢያ) ሙስሊሞች መቀየር ነው፡፡ ይህ ከሰዑዲ አረብያ፣ ከኳታር እና ከቱርክ ኤክስፖርት የሚደረግ አስተሳሰብ ተፅዕኖ በአገራችን ውስጥ እየጎላ ይገኛል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሱሪያቸውን የሚያሳጥሩ፣ ጢማቸውን የሚያንፍሩ፣ ግንባራቸውን የሚያጠቁሩ፣ ፊታቸውን ጨምሮ ሰውነታቸውን በጥቁር ልብስ የሚሸፍኑ፣ ሙስሊም ካልሆነው ማሕበረሰብ ራሳቸውን የሚነጥሉ፣ ከኢትዮጵያዊ ባሕል ይልቅ አረባዊነትን የሚከተሉ ሙስሊሞች በከፍተኛ ሁኔታ በአገራችን ውስጥ እየተበራከቱ መምጣታቸው በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያን ሙስሊሞች እንደገና የማስለም ዘመቻ ውጤት ነው፡፡ በዚህ መርሃ ግብር መሠረት እስልምናን የተማሩት ሙስሊሞች በአገራችን ውስጥ ምን ያህል ችግር እየፈጠሩ እንደሆነ ለማወቅ በጅማ፣ በባሌና በሐረር በክርስቲያኖች ላይ የተፈፀሙትን ጭፍጨፋዎችና ስደቶች ማስታወስ ብቻ በቂ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በአንፃራዊነት በመቻቻልና አብሮ በመኖር የሚያምኑት እስልምና የሰላም ሃይማኖት በመሆኑ ሳይሆን በእስልምና አስተምህሮ

በሚገባ ስላልተጠመቁ ነው፡፡ በእርግጥ የኢትዮጵያዊነት ስሜትና ሥነምግባር በጣም ጠንካራ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመቻቻልና አብሮ የመኖር ባሕላችንን የጥላቻና ሌሎችን የመግፋት ባሕል በሆነው የእስልምና ትምህርት እንዲለውጡ ለማድረግ እስላማውያን በብርቱ መጣር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የእስላማውያን የኢትዮጵያን ሙስሊሞች ከእንደገና የማስለም ዘመቻ እስኪሳካ ድረስ ገና ጥቂት ጊዜ የሚቀረን ይመስላል፡፡ ጥረቱ እስኪሳካ ድረስ የአይኤስን/ የእስልምናን ተግባራት ከልባቸው የሚኮንኑ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ይኖሩናል፡፡ ማምሻም እድሜ ነው፡፡

የአይኤስ ተግባራት እስላማዊ መሆናቸውን የሚያውቁና አይዲዮሎጂውን የሚቀበሉ ነገር ግን አይኤስን በምላሳቸው የሚኮንኑ ሙስሊሞች ደግሞ አሉ፡፡ እነዚህ የአስመሳይነት ባህሪ ያላቸውና ምቹ ጊዜ እስኪመጣላቸው ድረስ ትክክለኛ ስሜታቸውን በመደበቅ በልባቸው አይኤስን እየደገፉና በድርጊቶቹም እየፈነደቁ በአፋቸው ግን ለሚድያ ፍጆቻ ተቃውሞን የሚያሰሙ ናቸው፡፡ አንድ ሙስሊም አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር መዋሸትና ሙስሊም ያልሆኑትን ሰዎች ማታለል እንደሚችል እስልምና ያስተምራል፡፡ በእስልምና ውሸት የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች በሸሪአ ህግ ተደንግገዋል፡፡ እነዚህ ቅዱስ ውሸቶች በሺአ ሙስሊሞች ዘንድ ታቂያ በመባል የሚታወቁ ሲሆን በሱኒ ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ ሙደራት በመባል ይታወቃሉ፤ ቴክኒካዊ ስያሜዎች የተሰጧቸው ሌሎች ብዙ የውሸት ዓይነቶችም አሉ፡፡[41]

በእርግጥ አይኤስን በተመለከተ እስልምናን በሚገባ የሚያውቁ ሙስሊም ሊቃውንት ሁሉ የዓለምን ሕዝብ እያታለሉ ነው፡፡ አደባባይ በመውጣት አይኤስን እንደሚቃወሙና ተግባራቱም እስላማዊ እንዳልሆኑ መግለፃቸው የግብዝነት መሆኑን ከሚያሳዩ ማስረጃዎች መካከል አንዱ እስከዛሬ ድረስ አይኤስን የሚኮንን አንድም ፈትዋ አለመውጣቱ ነው፡፡ ፈትዋ ሙስሊም ሊቃውንት (ኡላማዎች) ቁርአንን፣ ሐዲሳትንና የነቢዩን ሱና በማጣቀስ የሚያወጡት እስላማዊ ድንጋጌ ነው፡፡ ፈትዋ አንዴ ከወጣ በኡላማዎቹ የአስተሳሰብ ጎራ ውስጥ የሚገኙ ሙስሊሞች ሁሉ ያለምንም ማንገራገር ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ሙስሊም ሊቃውንት አይኤስን በተመለከተ ፈትዋ ቢያወጡ ኖሮ ጥያቄ የሌለው እስላማዊ ድንጋጌ ስለሚሆን የአይኤስ ተግባራት እስላማዊ አይደሉም ብሎ ለመናገር ያስደፍር ነበር፡፡ እስከዛሬ ድረስ ሙስሊም ሊቃውንት በረመዳን ወር በዓለም የእግር ኳስ ጫወታዎች ላይ ለመሳተፍ ምግብን ከሙብላት ጀምሮ ፀረ እስላም ናቸው የሚባሉትን ግለሰቦች እስከመግደል ድረስ ባሉት ጉዳዮች ላይ ፈትዋዎችን አውጥተዋል፡፡ ነገር ግን የአይኤስን ተግባራት የሚኮንን አንድም ፈትዋ አላወጡም፡፡ መቼም ቢሆን እንዲህ ዓይነት ፈትዋ ሊያወጡ የሚችሉም አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የአይኤስ ተግባራት ፍፁም እስላማዊ ናቸውና፡፡ ነገር ግን ለሚድያ ፍጆታ ሲሉ አፍአዊ ተቃውሟቸውን ያሰማሉ፡፡ የዓለምንም ሕዝብ ያወናብዳሉ፡፡ የእስልምናን ባሕሪ የሚያውቁ ሰዎች በእንደነዚህ ዓይነቶቹ የይስሙላ እና የሸንገላ ተቃውሞዎች አይታለሉም፡፡

[41] *"ሙደራት"* የሱኒ የአታላይነት አስተምህሮ ነው፡፡ በሺአ ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ *"ታቂያ"* በመባል ይታወቃል፡፡ ከኡላማ ወይንም ከእስልምና ሊቃውንት ክበብ ውጪ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ስለዚህ አስተምህሮ አያውቁም፡፡ ሙደራት ማለት ማደናነቅ፣ የግብዝነት አድናቆት፣ ማታለል፣ ቆዳን ማስወደድ፣ ማጭበርበር፣ እኩል መራመድ፣ መሸፈን፣ መደበቅ ወይንም መሰወር ማለት ነው፡፡ ይህ የማታለል ጠባይ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ሰዓት ሁሉ በማንም ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን *የሱኒ ምሑራን* በቋሚነት *የሙደራት ዒላማ* ውስጥ መግባት አለባቸው ያሏቸውን አሥር ዓይነት ሰዎች ለይተው አስቀምጠዋል፡፡ *ካፊር* (ሙስሊም ያልሆነ ሰው)፣ ክፉ የሆነ መሪ፣ አዲስ የሰለሙ ሰዎች፣ ከእስልምና ልቡ ያፈነገጠውን ሰው ወደ እስልምና ለመመለስ፣ አማኞች ያልሆኑትን በመምሰል የሳተ ሙስሊም፣ የተማረን ሰው ወይንም ሳይንቲስት ከዕውቀቱ ለመጠቀም፣ ጓደኛን ለማስደሰት፣ ከጠላት ለማምለጥ ወይም ለመጉዳት፣ የትዳር አጋርን ለማስደሰት፣ የታመመ ሰው (ለምሳሌ ያህል ደህና እንደሚሆን ወይንም ደህና መምሰሉን በመንገር)፡፡ *የሱኒ ሊቃወንት* ይህንን አመለካከት ለማፅደቅ የተለያዩ የቁርአን ጥቅሶችን ይጠቅሳሉ፡፡ (Sam Solomon & E. Al-Maqdisi: *Al-Hijra, Islamic Migration,* 2009, pp. 72-79)

❺

## ፖለቲከኞች አይኤስ እስልምናን እንደማይወክል ስለምን ይሰብካሉ?

ብዙ የዓለም መሪዎች ሽብርተኝነት ከእስልምና ጋር በፍፁም እንደማይያያዝ አጥብቀው ይናገራሉ፡፡ በተለይም ክርስቲያን ወገኖች የሽብርተኞች ሰለባ ሲሆኑ በእምነታቸው ምክንያት ግፍ እንደተፈፀመባቸው ለመናገር የሚፈልጉ አይመስሉም፡፡ ባራክ ኦባማና መንግሥታቸው በአይኤስ እጅ የተገደሉትን ሃያ አንዱን ግብፃውያን ክርስቲያኖች የግብፅ ዜጎች መሆናቸውን እንጂ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ለመጥቀስ ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ የአገራችንም ሚድያዎችም የተሰውትን ሰላሳዎቹን ወገኖቻችንን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በማለት ከመጥራት ይልቅ የአገራችን ዜጎች፣ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ወዘተ. በማለት መጥራትን መርጠዋል፡፡

ፖለቲከኞች የእስልምናን ኢ-ሰላማዊነት የማይናገሩባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የመጀመርያው ስለ እስልምና አለማወቅ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ፖለቲከኞች እንጂ የሥነ መለኮት ሊቃውንት አይደሉም፡፡ በትምህርት ዘርፎቻቸው ልቅና ስላላቸውና ትልቅ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ በሥነ መለኮታዊ አስተምህሮቶች የተለወሰውን የእስልምናን ፖለቲካ በጥልቀት የመረዳት ችሎታ ይኖራቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ፍርሃት ነው፡፡ ለጥቂት ዓመታት የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ በመሆን ያገለገሉት ጳጳሱ ቤኔዲክት በ2006 በሬጌንስበርግ እያስተማሩ ሳሉ መሐመድ ሃይማኖቱ በሰይፍ እንዲስፋፋ ትእዛዝ እንደሰጠ የቢዛንታይን ንጉሥ የነበረው ዳግማዊ ማኑኤል ፓሌኦሎጎስ የተናገረውን በመጥቀስ ተናግረው ነበር፡፡ ይህንን ንግግር ተከትሎ በመላው የሙስሊም ዓለም ምን ዓይነት ገሃነመ እሳት ፈንቅሎ እንደወጣ እናስታውሳለን፡፡ በርግጥ ይህ ንግግር በመማር ማስተማር መካከል የተጠቀሰ እንጂ እስልምናን ለመንቀፍ ታስቦ የተነገረ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ፅንፈኛ ሙስሊሞች ሕይወትን በማጥፋትና ብዙ ጉዳቶችን በማድረስ ቁጣቸውን ገልፀዋል፡፡ ፅንፈኛ ሙስሊሞች እንዲህ ናቸው፡፡ እስልምና የሰላም ሃይማኖት አይደለም ብላችሁ ብትናገሩ የሰላም ሃይማኖት መሆኑን ሁከትና ሽብርን በመፍጠርና ሰላምን በማደፍረስ ያስረዱዋችኋል፡፡ ስለዚህ ፖለቲከኞች እስልምና የሰላም ሃይማኖት አለመሆኑን በልባቸው ቢያውቁ እንኳን ይህንን እውነት በአደባባይ ቢናገሩ ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ ስለሚፈሩ አይናገሩም፡፡ ነገር ግን እስልምና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን በመግለፅና ሙስሊሞችን በማስደሰት የእስልምናን ነውጠኛ ትምህርት ማለዘብ የሚችሉ ይመስላቸዋል፡፡ ወዳጆቼ ሆይ ይህ ከንቱ ተስፋ ነው፡፡ እስልምና የነዚህን ፖለቲከኞች ሙገሳ ማሕበረሰቡን ለማደንዘዝ ይጠቀምበታል እንጂ መቼም ቢሆን የአሸባሪነት ባህሪውን አያሻሽልም፡፡ እስልምናን በማሞጋገስና የሰላም ሃይማኖት መሆኑን በመስበክ ልንለውጠው አንችልም፡፡ ይህ ክርስቶስ ሳምራ ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ እንደሞከረችው ዓይነት ፍሬ አልባ ልፋት ነው፡፡ አደገኛነትም አለው፡፡ ይልቅስ የሙስሊሞችን ቁጣ ሳይቀሰቅሱ አክራሪ እስልምና የሚሸነፍበትንና የሁከት አይዲዮሎጂውም የሚከሽፍበትን ሌላ መንገድ መፈለጉ የተሻለ ነው፡፡

6

## መፍትሄው ምንድነው?

የእስላማዊ ሽብርተኝነት አይዲዎሎጂ የዓለምን ሕዝቦች እንደ ጭንቁር እየበላ ይገኛል፡፡ ዛሬ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚኖሩ ሕዝቦች ከእስላማዊ ሽብርተኝነት ስጋት ነፃ አይደሉም፡፡ ቸልተኝነቱ በዚህ ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ አንድ ቀን በፀፀት የማይቀለበስ አስከፊ ውጤት መከተሉ የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ሳይመሽ መፍትሄ መፈለጉ ግድ ይላል፡፡ ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ከሆኑ በኋላ ደም ማልቀስ ድንጋይ መንከስ፣ በቁጭት መብሰክሰክ ትርጉም አይኖረውም፡፡

ማሕበረሰባችንን ከዚህ አስከፊ የጥፋት ማዕበል ለመታደግ የመጀመርያው እርምጃ መሆን የሚገባው የችግሩን ምንጭ ለመረዳት ጥረት ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ወቅት የምንጊዜም ምርጥ ሳይንቲስት የሆነው አንስታይን ዓለምን ከጥፋት ለመታደግ አንድ ሰዓት ብቻ ቢሰጠው የተሰጠውን ጊዜ እንዴት እንደሚጠቀም ተጠይቆ ሲመልስ 55 ደቂቃዎችን ችግሩን ለመረዳትና 5 ደቂቃዎችን ብቻ መፍትሄ ለማፈላለግ እንደሚጠቀም ተናግሮ እንደነበር ይነገራል፡፡ የብዙ ችግሮቻችን መፍትሄ ያለማግኘት ምክንያቱ ችግሮቹን ራሳቸውን በትክክል አለማወቃችን መሆኑ እሙን ነው፡፡ ሽብርተኝነት በህዝባችን ላይ አደጋን የደቀነ የዘመናችን ተግዳሮት መሆኑን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን የሽብርተኝነት ምንጭ ምን እንደሆነ ስለማናውቅ የችግሩ አሳሳቢነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ አገራችን በዙርያዋ ከሚገኙት ጎረቤቶችዋ ጋር ሊነፃፀር በማይችልበት ሁኔታ ከሽብር አደጋዎች ተጠብቃ ትገኛለች፡፡ ነገር ግን የሽብርተኝነት ምንጭ የሆነውን የአክራሪ እስልምናን ትምህርት በትክክል ተረድተን መፍትሄ ካላፈላለግን በስተቀር ይህ አንፃራዊ ሰላም በዚህ ሁኔታ ለመቀጠሉ ምንም ዋስትና አይኖረንም፡፡ ስለዚህ ዜጎችም ሆንን መሪዎች አክራሪ እስልምና ሽብርተኝነትን በተመለከተ ምን እንደሚያስተምር፣ ምን እንደሚያቅድ፣ የአፈፃፀም ስልቶቹ እንዴት እንደሆኑ፣ ወዘተ. ማጥናት ያስፈልገናል፡፡ እውቀቱ ካላቸው፣ በተለይም ደግሞ በእስልምና ትምህርቶች ከሰለጠኑና እስልምናን ለቀው ከወጡ ሰዎች መማር እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

## ትክክለኛ መፍትሄ የሚገኘው በማን እጅ ነው?

አንዳንዶች አክራሪ እስልምና ፖለቲካዊ ችግር በመሆኑ መፍትሄው ፖለቲካዊ ነው ስለዚህ ችግሩ ለመንግሥት ብቻ መተው አለበት ይላሉ፡፡ ነገር ግን፡-

- መንግሥት ሥልጣንና ጉልበት ቢኖረውም የትምህርቱን ውጤት እንጂ ትምህርቱን መጋፈጥ አይቻለውም፡፡ የመንግሥት አካላት ብዙ ጊዜ በሃይማኖት ካባ ተሸፍኖ ለክፍለ ዘመናት የኖረውን የእስልምናን ፖለቲካ ለመረዳት ሲቸገሩ ይስተዋላል፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ መፍትሄ ለመስጠት ይቸገራሉ፡፡
- የመንግሥት አካላት የነገሩን ውስጠ ሚስጥር ቢረዱትም እንኳን መንግሥት ሁሉን አቀፍ በመሆኑ ገለልተኛነትን ይመርጣሉ፡፡ ስለዚህ የችግሩ መንስኤ የሆነውን የእስልምናን መሠረት መንካት አይፈልጉም፡፡
- አክራሪ እስልምና አይዲዮሎጂ በመሆኑ በጉልበት አይቀለበስም፡፡ አንድ ትምህርት ወይም ፍልስፍና አንዴ ወደ ሰዎች ሕይወት ገብቶ ተከታዮችን ካገኘ በኋላ በጦር መሳርያ ኃይል ሊቀለበስ እንደማይችል ከዓለም ታሪክ መረዳት እንችላለን፡፡ በኃይል ተጨፍልቆ የጠፋ ቢመስልም እንኳን

ምቹ ጊዜ ጠብቆ ብቅ ማለቱ አይቀርም፡፡ አንድን ትምህርት ወይም ፍልስፍና ሊቀለብስ የሚችለው ከእርሱ የተሻለ ትምህርት ወይም ፍልስፍና ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ መንግሥት አክራሪ እስልምና የጦር መሳርያ ይዞ አደባባይ ሲወጣ በጦር መሳርያ ማስታገስ ቢችልም ነገር ግን ትምህርቱን የሚጋፈጥበት ሁነኛ መሳርያ የለውም፡፡

- ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደታዘብነው አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይባስ ብለው ከአክራሪ እስልምና ጋር በመተባበር አጀንዳውን ሲያራግቡና ጥብቅና ሲቆሙለት ታይተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አንዳንድ ፖለቲከኞች የዛሬ ጥቅማቸውን እንጂ የነገውን አደጋ ማየት አለመፈለጋቸውን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ሥልጣን ቢይዙ ችግሩን ከማባባስ ውጪ መፍትሄ መስጠት አይችሉም፡፡

- የመገናኛ ብዙኃንን ስንመለከት እንኳንስ መፍትሄ ሊሰጡ ይቅርና ጥያቄውን እንኳ በትክክል የተረዱት አይመስልም፡፡ በትክክል ቢረዱትም እንኳን ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ስለሚጫናቸው የችግሩን ስረ መሠረት በመንካት መፍትሄ ማፈላለግ አይሆንላቸውም፡፡

- ምሑራን ጥያቄውን የተወሰነ ያህል ይረዱታል ነገር ግን የችግሩን ስረ መሠረት በመጥቀስ የመፍትሄ ሐሳቦችን እንዳይሰነዝሩ በፍርሃትና በፖለቲካዊ ትክክለኝነት ተሸብበዋል፡፡

አንዳንድ ለዘብተኛ አመለካከት ያላቸው ምዕራባውያን የሚከተሉትን "መፍትሄዎች" ያስቀምጣሉ፡-

- ለአክራሪ ሙስሊሞች ምንም ትኩረት አለመስጠትና ችላ ማለት፡፡
    - ነገር ግን ችላ የሚባሉት እምን ድረስ ነው? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ሰይፍ አንገታችን ላይ ተቀምጦ "ትኩረት አንሰጠውም" ማለት የሞኝ መፍትሄ ነው፡፡
- ባሉበት እንዲሆኑ ማገድ (ወደ ክልላችን እንዳይገቡ ማድረግ፡፡)
    - አሁን ካለው የሕዝቦች እንቅስቃሴና የመረጃ ቴክኖሎጂ ደረጃ አኳያ አያስኬድም፡፡ የውጪዎቹ እንዳይገቡ ማገድ ይቻል ይሆናል፣ ውስጥ የሚገኙትንስ? መግደል? ማሰር? ከሃገር ማባረር? አያዋጣም፡፡
- እስልምናን ከፖለቲካዊ ይዘቱ በማፋታት ምዕራባዊ መልክ ያለውን እስልምና መፍጠር [ለምሳሌ ኪሊያም (Quilliam) ፕሮጀክት]፡፡[42]
    - የእስልምና ቅዱሳት መጻሕፍት እስካልተለወጡ ድረስ ይህንን ማድረግ አይቻልም፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት እንዲህ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ሆነው አልታዩም፡፡
- ጥብቅ ህጎችን በማውጣት ወይም በጠብመንጃ አፈሙዝ በመጠቀም ማጥፋት፡፡
    - ጥብቅ ህጎችን ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ነገር ግን በነዚህ ህጎች ተጠቅሞ ለዚህ አይዲዮሎጂ ተጋላጭ እንዳይሆኑ ከማድረግ አኳያ የሰዎችን የግል ሕይወት መቆጣጠር የሚቻለው እስከምን ድረስ ነው? አይዲዎሎጂስ በጠብመንጃ አፈሙዝ ሊጠፋ ይችላልን?

ዘላቂና አዋጭ የሆነ መፍትሄ ከላይ ከተጠቀሱት አካላት ዘንድ እንደሌለ ተመልክተናል፡፡ አክራሪ እስልምናን መከላከል የሁሉንም አካላት ርብርብ የሚጠይቅ ቢሆንም ነገር ግን በሚከተሉት ምክንያቶች ለዚህ ችግር መፍትሄው በዋናነት በቤተ ክርስቲያን እጅ ይገኛል፡-

† **እኛ ክርስቲያኖች አክራሪ ሙስሊሞችን በትክክል እንረዳቸዋለን**

[42] http://www.bbc.co.uk/religion/0/24706419
http://www.wikipedia.org/wiki/Quilliam_(think_tank)

- *መነሻ መሰረታችን ተመሳሳይ ፅንሰ ሐሳብ ያለው አስተሳሰብ ነው፣ ማለትም ሃይማኖት ነው:: (በቅዱሳት መጻሕፍት እናምናለን:: በእምነቶቻችን ውስጥ እንደ ሞዴል የምናያቸው ስብዕናዎች አሉን፤ ኢየሱስና መሐመድ)::*

† ***መሳርያዎች አሉን***
  - *የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች አሉን::*
  - ክርስትና ከእስልምና የላቀ *ታሪካዊ መሠረት* አለው::
  - ኢየሱስ ከመሐመድ የላቀ *የሥነ ምግባር* መርሆችን አስተምሯል (በበቀል ፋንታ ይቅርታን፣ ጠላቶቻችንን መውደድ፣ ወዘተ.)::
  - *ሙስሊሞች ስለ እምነታችን ካላቸው እውቀት ይልቅ እኛ ስለ እነርሱ እምነት ያለን እውቀት የተሻለ ነው:: በሥነ መለኮት ትምህርትቤቶቻችን ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተደራጁና እስልምናን በጥልቀት ባጠኑ ሊቃውንት የሚመሩ የትምህርት ክፍሎች አሉ:: በእስልምና ትምህርት ቤቶች ግን ይህንን አናገኝም::*
  - በአገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ክርስትና ከእስልምና የበለጠ የሰው *ኃይል* አለው::
  - *የመንፈስ ቅዱስ ኃይል* አለን (በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ድንቅና ተዓምራት አሉ:: በእስልምና ግን ይህ የለም)::

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት ወስዳ ለመስራት መዘጋጀት ይኖርባታል::

# ከክርስቲያኖች ምን ይጠበቃል?

1. ***<u>ሙስሊሞችን መውደድ</u>* :-** የክርስቶስ *መንገድ* የፍቅር *መንገድ* ነው:: እኛ ውጊያችን ከደምና ከሥጋ ጋር ስላልሆነ አክራሪ እስልምናን እንጂ ሙስሊሞችን ልንቃወም አይገባንም:: ለሰይፍ መልስ ሰይፍ የምንመዝ ከሆነ ውድቀታችንን እናፈጥናለን:: ምንም ያህል ኢ-ምክንያታዊ ቢመስልም ለሰይፍ በሰይፍ ምላሽ መስጠት ክርስቲያናዊ መርህ አይደለም:: ክርስቲያናዊ መርህ ፍቅርና ይቅርታ ነው::

   *"ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።" (ዮሐንስ 3፡16)*
   *"ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ።" (ሉቃስ 6፡26-27፣ በተጨማሪም ማቴ 5፡38-48፣ ማርቆስ 12፡29-31፣ ሮሜ 13፡8፣ ሌዋ. 19፡16-18)*

   በርግጥ አክራሪ እስልምና የክርስቲያኖችን የፍቅርና የትህትና ምላሽ እንደ ውርደትና እንደሽንፈት ነው የሚቆጥረው:: ቢሆንም ግን ከዚህ የክርስቶስ መርህ መውጣት አልተፈቀደልንም:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ቢሊዮን በላይ ተከታዮችን ያፈራውና የሮምን ኢምፓየር ከእግሩ በታች ያንበረከከው ሽንፈት በሚመስል የፍቅር ምላሽ ነበር:: የምንጎዳ መስሎ ቢሰማንም እንኳ ይህንን የክርስቶስን መርህ መከተል ግድ ይለናል:: ሙስሊሞችን እንውደዳቸው፣ እንዘንላቸው፣ ደግ እንዋልላቸው፣ መልካም ጎረቤቶች እንሁናቸው፣ እውነትን በፍቅር እንንገራቸው:: ፍቅር ተሸናፊ ቢመስልም ምን ጊዜም አሸናፊ ነውና::

2. ***<u>እውነትን መናገር</u>* :-** ክርስቲያኖች የፍቅር ሰዎች መሆን እንደሚገባቸው ሁሉ ለእውነት የሚቆሙ ሰዎችም መሆን ይገባቸዋል:: እስልምናን በተመለከተ "እስላም ሰላም ነው"፣ "ቁርአን የሰላም መጽሐፍ ነው"፣ "ሽብርተኝነት ከእስልምና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም"፣ "እስልምና በሰይፍ አልተስፋፋም"፣ "ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች አንድ ዓይነት አምላክ ነው የሚያመልኩት"፣ "የግራኝ መሐመድ ጦርነት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አልነበረም"፣ ወዘተ. የሚሉትን የውሸትና የሽንገላ ንግግሮች መቀበል የለብንም:: ፍቅር ማለት እውነትን ማለባበስ ማለት አይደለምና:: በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የፍቅር አንዱ መገለጫ እውነትን መናገር ነው (1ቆሮ 13፡6):: ውሸትና ሽንገላ የፍቅር መገለጫ ሊሆን አይችልም:: በጥበብ በመመላለስና እንደ ጠቢባን በመናገር ለእውነት ዘብ ልንቆም ይገባናል::

3. **ፍርሃትን አውጥቶ መጣል** ፡- ሙስሊም ሽብርተኞች አሳቃቂ ቪድዮዎችን እየቀረፁ የሚለቁበት ዋናው ምክንያት ፍርሃትና ሽብርን ለመንዛት ነው፡፡ ከፈራንላቸው ዓላማቸው ግቡን መቷል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አለመፍራታችንን በተግባር በማሳየት ዓላማቸው መክሸፉን ልናሳውቃቸው ይገባል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች መጪውን አደጋ ከመከላከል አንፃር የችግሩን መንስኤና ታሪካዊ ሂደቱን በማወቅ መፍትሄ ለማፈላለግ እንጂ እንድንፈራና ሙስሊም ጎረቤቶቻችንን በጥርጣሬ እንድንመለከት አይደለም፡፡

*"ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።" (1ዮሃ 4፡18)*

4. **መጸለይ** ፡- ጸሎት በቃላት የማይነገር ኃይል ያለው ትልቅ የክርስቲያን መሣርያ ነው፡፡ አክራሪ እስልምና የሰው ፍልስፍና ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ከበስተጀርባው ሆኖ የሚሠራበት አስተሳሰብ ነው፡፡ ክርስቲያኖች በጸሎት የምንተጋ ከሆነ ከበስተጀርባው የሚሠራውን ክፉ መንፈስ በማሰር አቅም ልናሳጣው እንችላለን፡፡ (ኤፌሶን 6፡10-18)
5. **ወንጌልን ለሙስሊሞች ማብሰር** ፡- የአክራሪ እስልምናን ንፅረተ ዓለም ማንኮታኮት የሚችለው ብቸኛ ንፅረተ ዓለም በእውነተኛው የክርስቶስ ወንጌል ላይ የተመሠረተው ክርስትና ነው፡፡ ሙስሊም አገራትንም ከምዕራባውያን የጦር መሣርያዎች ይልቅ ብርክ የሚያሲዛቸው የክርስቶስ ወንጌል ነው፡፡ ወንጌል የእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ኃይል ደግሞ መቋቋም የሚችል ምንም ዓይነት ኃይል የለም፡፡ አክራሪ እስልምና አቅም የሚያገኘው እኛ ወንጌልን ከመስበክ ወደ ኋላ ስንል ነው፡፡ ሽብርተኝነትንም የሚጠቀመው ወንጌልን የመቋቋም አቅም ስለሌለው ነው፡፡ የወንጌሉን ብርሃን ይዘን ወደ ጨለማው ዓለም በመሄድ የታሰሩትን ነፃ ማውጣት የኔና የናንተ ድርሻ ነው፡፡ አምላካችን ደግሞ ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ተስፋን ሰጥቶናል፡፡ *(ማቴ 27፡18-20)*

   ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስባታሊ ጉዳዮቻችን ከወንጌል ጋር ያልተያያዙ ሥጋዊ ጉዳዮች መሆናቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ነው፡፡ በጎጠኝነትና በምድራዊነት እግረሙቅ ስለታሰርን የጨለማው ግዛት እየሰፋ እኛ ግን መብራቱን ይዘን መሄድ ተስኖናል፡፡ የረሳነውን ተልዕኳችንን እናስታውስ፤ በአጭር ታጥቀን የጌታችንን ትዕዛዝ ለመፈፀም እንነሳ፡፡ ትውልዱን እንታደግ፡፡
6. **አቃቤ እምነታዊ አገልግሎትን ማበረታታት** ፡- እስልምና በክርስትና ላይ ትችቶችን ያለማቋረጥ ይሰነዝራል፡፡ ቁርአን የክርስትናን አስተምህሮዎች በሚያንቋሽሹ ትምህርቶች የተሞላ ነው፡፡ ሙስሊሞችም ደግሞ በየጊዜው መጽሐፍ ቅዱስንና የክርስትናን መሠረታዊ ትምህርቶች የሚያብጠለጥሉ ጽሑፎችንና ቪዲዮዎችን እያሳተሙ ያሰራጫሉ፡፡ ለእነዚህ ትችቶችና ጥያቄዎች የማያዳግም ምላሽ ለመስጠት መትጋትና ሕዝባችንንም በዚህ ማስታጠቅ ያስፈልገናል፡፡ በአቃቤ እምነት አገልግሎት ላይ የተሰማሩትንም ወገኖች አስፈላጊ በሆነው በማንኛውም መንገድ በመደገፍ ማበረታታት ያስፈልገናል፡፡ *(1ጴጥ. 3፡15፣ 1ቆሮ 10፡4-6፣ ፊልጵ. 1፡7፣ ይሁዳ 3)*
7. **ክርስቲያኑን ማህበረሰብ በኢኮኖሚ ለማጠናከር መሥራት** ፡- ለክርስቲያኖች የሥራ ዕድሎችን መፍጠር፣ ከክርስቲያን ነጋዴዎች ላይ መግዛት፣ ተደራጅቶ አንድ ላይ መስራት፣ መረዳዳት፣ ወዘተ. ያስፈልገናል፡፡ (ሮሜ 12፡13)
8. **ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻችንን በትክክል ማወቅና መጠቀም** ፡- ሕገ መንግሥታችን የሰጠንን መብቶች አሟጠን በመጠቀም መብቶቻችንን በማስከበር ከእስላማዊ ጭቆና ራሳችንን ነፃ ማድረግ ያስፈልገናል፡፡ ከሕገ መንግሥቱ ውጪ እስልምናን ለመጥቀም የሚፈፀሙ በደሎች ካሉ አስፈላጊውን የሕግ አካሄድ ሁሉ በመጠቀም መብታችንን ማስከበር ያስፈልገናል፡፡ በዞንና በክልል ደረጃ የሚፈፀሙ ፍትህን የማጉደል ተግባራትን ትክክለኛውን አካሄድ በመጠቀም እስከ አገሪቱ ዋና መሪዎች ድረስ የመውሰድ ፅናት ሊኖረን ይገባል፡፡ *(ሐዋ 16፡35-39፣ ሐዋ 24፡9-12)*

9. **ክርስቲያኖች አንድ መሆን** ፡- እስልምና የክርስትና ቤተ እምነቶችን ነጣጥሎ የመምታት አካሄድ አለው፡፡ ለምሳሌ ያህል በጅማ ዞን የተፈፀሙትን የሽብር ጥቃቶች ስንመለከት መጀመርያ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮችን ነጥሎ የማጥቃት ሁኔታ ነበር፤ ከዝያ በኋላ ደግሞ ሰበብ ፈልጎ ፕሮቴስታንቶችን ብቻ የማጥቃት ዘመቻ ተደርጎ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ለእንዲህ ዓይነት መሰሪ እስላማዊ አካሄዶች መመቸት የለባቸውም፡፡ የክርስቶስን መስቀል ምልክቱ ያደረገ የትኛውም ማሕበረሰብ ሲጠቃ በአንድነት መቆም ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት የጋራ አንድነትን በመፍጠር እስላማዊውን ተግዳሮት መጋፈጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ዘመኑ ልዩነቶቻችንን የምናጎላበት ዘመን ሳይሆን ሜዳውን ለማዳን የምንረባረብበት ዘመን ነው፡፡ ይህንን በማድረግ ረገድ ከመሪዎቻችን ትልቅ ሥራ ይጠበቃል፡፡

10. **ጥቃት ሲፈፀም ድምፃችንን በጋራ ማሰማት** ፡- እስላማዊ የሽብር ጥቃቶችና በደሎች ተድበስብሰው መቅረት የለባቸውም፡፡ ሙስሊሞች ችግር ከፈጠሩ በኋላ ነገሩ ተድበስብሶ እንዲቀር ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን አስፈላጊው የፍትህ እርምጃ እስካልተወሰደ ድረስ ተመሳሳይ ችግር መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ብዙ ጊዜ ሙስሊም ሽብርተኞች የሆነ በደል ይፈፅሙና ይፈትሹናል፡፡ ምላሻችን የቸልታና የተቀዛቀዘ ከሆነ የባሰ ጥቃት ይፈፅማሉ፡፡ ክርስቲያናዊ ፍቅርና ይቅርታ ማለት ወንጀለኞች እንደ በግ ሲያርዱን ሲወስዱን ዝም ብሎ መነዳት ማለት አይደለም፡፡ "ቀኝህን ለሚመታህ ግራህን ስጠው" የሚለውም ቃሉን አንብበው ሊመቱን የሚመጡ ሰዎች እንዲያላግጡብን የተጻፈ አይደለም፡፡ ሚዛናዊ መሆን ያፈልገናል፡፡

**ሕጋዊ አካሄዶችን ብቻ መከተል** ፡- በፅንፈኛ ሙስሊሞች ለሚፈፀሙ በደሎች ክርስቲያኖች ምላሽ መስጠት ያለባቸው ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንጂ ፍትህን በራሳቸው እጅ ለመፈፀም በመሞከር በህገወጥ አካሄድ መሆን የለበትም፡፡ እንደዚያ ዓይነቱ አካሄድ ለአገር ሰላም አይበጅም፡፡ ክርስትናንም ያስነቅፋል፡፡ ነገር ግን ሰይፍን እንዲታጠቅ እግዚአብሔር የሾመው ተቋም አለ፡፡ ይህም ተቋም መንግሥት ነው፡፡ በመንግሥት ለሚወሰድ የፍትህ እርምጃ እግዚአብሔር እውቅናን ይሰጣል፡፡ በደለኞችን ለመቅጣት የእግዚአብሔር መሳርያ እንደሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ስለዚህ በደል ሲፈፀም እግዚአብሔር በደለኞችን እንዲቀጣ ለሾመው አካል ለመንግሥት ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡ *(1ጴጥ 2፡13-14)*

11. **ህፃናትና ወጣቶች ላይ ትኩረት በማድረግ መስራት** ፡- ልጆቻችንን በሚገባ በእግዚአብሔር ቃልና በዕውቀት ኮትኩተን ካላሳደግን እንዲሁም ወጣቶቻችንን በሚገባ ካላስተማርን አገሪቱን ለሌላ ለማስረከብ እየተዘጋጀን ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለህፃናትና ለወጣቶች ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት መሥራት ይጠበቅባታል፡፡ *(ምሳሌ 22፡6)*

12. **የአገሪቱን የክርስትና ታሪክ ማጉላት** ፡- በአሁኑ ወቅት የክርስትና እሴቶች በጣም በረቀቀ ሁኔታ ከአገሪቱ አደባባዮች እየተወገዱ ይገኛሉ፡፡ ክርስትናን የሚገልፁ ምልክቶች እየተለወጡ ይገኛሉ፡፡ ከመማርያ መጻሕፍትም ውስጥ የክርስትና እሴቶችና ታሪኮች ቀስ በቀስ በመውጣት በእስላማዊ እሴቶችና ታሪኮች የመተካት ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ክርስቲያኖች ይህንን አካሄድ ለማስቆም መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

13. **ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ ከመንግሥት ጋር በመተባበር መሥራት** ፡- መረጃዎችን በማቀበልና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ከመንግሥት ጎን መቆም አስፈላጊ ነው፡፡ የፖለቲካ አሰላለፋችን በየትኛውም ጎራ ይሁን ነገር ግን በዚህ ረገድ ከመንግሥት ጋር መተባበር ይኖርብናል፡፡ ከሽብርተኝነት ጋር የሚደረጉ ትግሎችን ፖለቲካዊ ማድረግ በእጅጉ የተሳሳተ አካሄድ ነው፡፡

14. **ክርስቲያኖች በፖለቲካው መስክ እንዲሳተፉ ማበረታታት** ፡- በአሁኑ ወቅት ሙስሊም ወገኖች ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ትልቅ ሩጫ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን መሳተፍ መብታቸው ቢሆንም ነገር ግን በፖለቲካው ውስጥ ከቁጥራቸው ጋር የማይመጣጠን ድርሻ መያዝ አይገባቸውም፡፡ አክራሪ ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ የክርስቲያኖችን መዘናጋት በመጠቀም የሥልጣን ወንበሮችን የመያዝ አካሄድ አላቸው፡፡ ክርስቲያኖች በሁሉም ረገድ በፖለቲካ ውስጥ በንቃት በመሳተፍ ክፍተቶችን ሁሉ መድፈን ይኖርባቸዋል፡፡

## ዋቢ ምንጮች


- Al-Tabari, *The History of al-Tabari (Ta'rikh al-rusul wa'l-muluk), Vol. VI:*
- Belteshazzar & Abednego. *The Mosque and Its Role In the Society:* 2006
- Campo, E. Juan. *Encyclopedia of Islam:* 2009
- Durie, Mark. *The Third Choice, Islam, Dhimmitude and Freedom:* 2010
- Gabriel, Mark A. *Islam and Terrorism:* 2002
- Guillaume, Alfred. *The Life of Muhammad: A Translation of Ishaq's Sirat Rasul Allah:* 1955
- Holy Qur'an, Abdullah Yusuf Ali's translation
- Ibn Sa'd al-Baghdadi: *The Book of the Major Classes Vol. 2*
- Ibn Sa'd. *Kitab al-Tabaqat al-Kkabir:* (Translated into English by S. Moinul Haqq) Vol. 2: 1972
- *Kitab al-Maghazi:* Translated by Faizer R., Ismail A., & Tayob, A. K.: 2011
- Maududi, Sayid abul A'La. *The meaning of the Qur'an:* Vol. 5
- Musnad Ahmed Ibn Hanbal http://www.kalamullah.com/musnad-ahmad.html
- *Sahih Albukhari:* Translated by Dr. Muhammad Mushin Khan, Vol. 1-9: 1997
- *Sahih Muslim:* Translated by Nasruddin al-Khattab, 2007
- Solomon, Sam & E. Almaqdisi: *Al Hijra, Islamic Doctrine of Migration:* 2007
- Sunan Abu Dawud http://www.sunnah.com/abudawud
- Sunan An-Nasa'i http://www.sunnah.com/nasai
- Sunan Ibn Majah http://www.sunnah.com/ibnmajah
- Tafsir of Ibn Kathir http://www.qtafsir.com
- *መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣* ኢንተርናሽናል ባይብል ሶሳይቲ፡ 1993
- *መጽሐፍ ቅዱስ፣* የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፡ 1954
- *ቅዱስ ቁርኣን፣ የአማርኛ ትርጉም፣* ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት
- ኢማም አን-ነወዊ፣ *ሪያዱ ሷሊሒን፣* ከሐዲስ ቁጥር 811-1896፣ ቅፅ 2፣ ትርጉም በሐሰን ታጁ

- http://www.catholic.org
- http://www.christianpost.com
- http://www.dailymail.co.uk
- www.dhimmitude.org
- http://www.frontpagemag.com
- http://www.geopolintelligence.com
- http://www.huffpost.co.uk
- http://www.raymondibrahim.com
- http://www.wikipedia.org
- www.answering-islam.org